# ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ) ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ለውይይት የቀረበ

## ፩. መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተሻለ አስተዳደር በልዩ ልዩ መልክ ታግሏል፤ በመታገልም ላይ ነው:: ከሐምሌ 19 እስከ ሐምሌ 26 ቀን 1995 ዓ/ም በሮክ ቪል ሜሪላንድ፥ አሜሪካ የተካሄደው የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ዐቢይ አገራዊ ጉባዔ ውጤት የሆነው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) መፈጠር ለብዙ በጎ አሳቢና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተስፋ መስጠቱ ይታመናል::

ኅብረቱን መመሥረት የተቻለውም የጉባዔው ተሳታፊ ድርጅቶች ሠፊ ውይይቶችና የሃሳብ ፍጭቶች በስፋትና በጥልቀት አካሂደው ለጋራ አገራዊ ዓላማ በጋራ ለመታገል ሙሉ በሙሉ በመስማማታቸው ነው::

እዚህ ላይ ኅብረቱን ለመመሥረት ያስቻሉ የጋራ ግንዛቤዎችን በአጭሩ መቃኘቱ መልካም ይሆናል::
ጉባዔው የአገራችንን ሁኔታ በተቀዳሚ የመወያያ ነጥብነት (አጀንዳነት) ተወያይቶ በሙሉ ድምጽ መግባባትና ስምምነት ላይ የደረሰባቸው የጋራ ግንዛቤዎች፤

*1. አገሪቱና ሕዝቧ በረዥም ጊዜ ታሪካቸው ከመቸውም ጊዜ የበለጠ አሳፋሪ፥ አስቃቂ፥ ዘግናኝና አስቸኳይ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊ ና ማኅበረሰባዊ ቀውሶች ውስጥ መሆናቸው፤*

*2. በሥልጣን ላይ ያለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ያለ ሕዝብ ነፃ ፍላጎት፤ ፈቃድና ምርጫ ወደ ሥልጣን የመጣ፥ ሥልጣን ላይ ያለና የሕዝብን አመኔታና አክብሮት ያጣ፥ የውጭ ጥቅም አስጠባቂና ፍጹም አምባገነን መሆኑ፤*

*3. አሁን በአገሪቱ ያለው "ሕገ-መንግሥት" ከአረቃቀቁ ሂደት ጀምሮ የሕዝብ ቀጥተኛና ነፃ ተሳትፎ የሌለበትና የአንድ ጎሠኛ ፓርቲ ሕግ መሆኑ፤*

*4. አገራችን የሕግ የበላይነት የማይከበሩባት፥ የዜጎች ሁለንተናዊ መብቶች የሚረገጡባት መሆኗ፤*

*5. የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት የአገሪቱንና የሕዝቧን ብሔራዊ ጥቅሞች የማያስጠብቅ ብቻ ሳይሆን እጅጉን የሚጻረሩ ተግባሮች ላይ የተሰማራ፥ ለመታረም ፈቃደኛ ያልሆነ አጥፊ ቡድን መሆኑ፤*

*6. አሁን ያለው የአገሪቱ ሁኔታ እንዲቀጥል ከተፈቀደ፥ አገራችን እንደ አገር፥ ሕዝቧም እንደሕዝብ መቀጠል የማይችሉበት እጅግ አደገኛ ሁኔታ ላይ መሆናቸው፤*

*7. በተቃዋሚነት የተሰለፉና የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ጠንካራና የጠራ ኅብረት ፈጥረው በጋራ ለመታገል በአለመቻላቸው የአገራችን የመከራና የሰቆቃ ዘመን እንዲቀጥል አስተዋጽዖ እንዳደረጉ፤*

*8. የባሰ አደገኛ የሆነውን የአንድ ሰው አምባገነንነትን እያጠናከረ የሚገኘው በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን እስከ አሁን ባሳየው አንድነት አፍራሽ፥ ደንታ ቢስ፥ ከሃዲና መብት ረጋጭ ባህርያትና ድርጊቶች፥ የአገራችንን ከባድና ውስብስብ ችግሮች ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከተቃዋሚው ክፍል ጋር በውይይት ለመፍታት ምንም ዓይነት ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ፤*

*9. በሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን በሥልጣን ላይ እንዲቆይ መፍቀድ አገሪቱ የምትገኝባቸው ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች እንዲቀጥሉ መፍቀድ በመሆኑ፥ ተቃዋሚው ክፍል ከሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመወገን በተባበረ ጥረትና በሰላማዊ ትግል ይኸን የጥፋት መልክተኛና ሃላፊነት የማይሰማው አካል ከሥልጣን አስወግዶ ሥልጣንን ለባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማስረከብ አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ ታምኖበታል::*

*ከዚሁ ጋር መጠቀስ የሚኖርበት ኅብረቱ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ለማስወገድ የሚከተለው የሰላም ትግል ነፃና ርቱዓዊ ምርጫን በማካሄድና ለዚሁ በሚያካሂደው ሕዝባዊ ትግል መሆኑን ነው::*

ከላይ የተዘረዘሩት በአጭር ሲጠቃለሉ ፥ አገራችንንና ሕዝቧን ወደ አለመኖር እየወሰዱ ያሉ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ብቃቱም ሆነ ፍላጎቱ የሌለው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ባለበት የሥልጣን ቦታ ላይ እስካለ ድረስ ሁኔታዎች ከመባባስ እንደማይቆሙ፥ በተቃዋሚው ጎራ የቆሙት ድርጅቶችም በምንም መልኩ በተናጠል በሚያራምዱት ትግል አዎንታዊ ምላሽ ማስገኘት እንደማይችሉ፥ ችግሮቻችንን መፍታት የምንችለው በጋራ በመቆም ብቻ እንደሆነ፥ የምንከተለውም የትግል ስልት ሰላማዊ ፥ መሣሪያችንም ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ መሆኑን እንገነዘባለን::
ኢዴኃኅንም ያቋቋምነው ለዚሁ የወል ዓላማ <u>የጋራ</u> <u>የመታገያ መድረክ</u> ሆኖ እንዲያገለግለን ነው::

ኅብረቱ ሲፈጠር በዝርዝር ያልታዩ፥ በበቂ ግልጽ ያልሆኑና አሻሚ የሆኑ፥ ማሰሪያ ያልተደረገላቸውና አንዳንድ በተግባር ለመተርጎም የሚያስቸግሩ ነጥቦች ሊኖሩ መቻላቸው ግልጽ ነው::
አንዳንዶቹ እንዲሁ ተረስተው የቀሩ አልነበሩም:: ቢያንስ ለአንዳንድ ተሳታፊ ድርጅቶች ግልጽ ይሆኑ ይሆናል የሚል እምነት አለን:: በኛ በኅብረሕዝብ በኩል ግልጽ ነበር::
ሆኖም በነበረው ቁጥር ዓይነት የመጀመሪያ ስብሰባ ስለነበርና በነበረው ጊዜና ከተሰብሳቢው ስብጥር አኳያ ከተደረሰበት የጋራ ስምምነትና አቋም የበለጠ ለማድረግ መሞከር "አጠብቅ ባይ በጣሽ" ስለሚሆን በመጠኑ አስቸጋሪ እንደሚሆን በበቂ ተገንዝበናል::
በኅብረሕዝብ እምነት አንድ ጊዜ በጣም መሠረታዊ በሆኑ የጋራ ጉዳዮች ላይ መግባባት ከተቻለና ስምምነት ኖሮ በአንድ የጋራ መድረክ ለመታገል ከተወሰነ፥ ትግሉ የተሚዘዘ ሳይሆን ሕይዎት ያለውና ሕዝብን ሊያንቀሳቅስ የሚችል ጥረት ከተደረገ፥ በአባል ድርጅቶች መካከል የተሻለ ትውውቅንና መግባባትን ማዳበር ያስችላል፤ መግባባት ሲበለጽግ ደግሞ የሁሉም ትኩረትና ርብርቦሽ በሚኖሩና ይኖራሉ ተብለው በታሰቡ "ልዩነቶች" ላይ ሳይሆን በጋራው ዓላማ ላይ እንዲሆን ሁኔታው ስለሚያበረታታ፤ ግልጽ ያልሆኑትና የተሻለ መብራራት የሚያስፈልጋቸውም ሆነ የነጠረ ግንዛቤ ሊወሰድባቸው የሚችሉ ነጥቦችን በሂደት ማከናወን ይቻላል በሚል ተስፋ ነው ብዙም ያልገፋንበት::
ይኸም ሁሉም በትግሉ ሥራዬ ብሎ ከተጠመደና ትኩረቱ በሃቅ በተደረሰው የጋራ ግንዛቤ መሠረት ለእውነተኛና ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት የተሻለ ሥርዓትን ሊወልድ የሚችል ለውጥ ላይ ከሆነ፥ መንገዱ አስቸጋሪና ጠመዝማዛ መሆኑን በሚገባ ብናውቅም፥ እንታገልልሃለን ለምንለው ሕዝብ የገባነውን ቃል ጠብቀን እንወጣዋለን ከሚል የጠና እምነት የመነጨ ነው::
ይሁንናም በታሰበውና በተመኘነው ልክ ኅብረታችን የተጧጧፈና ሕይዎት ያለው እንቅስቃሴ ማድረግ አልተቻለውም:: ኅብረቱ ትግሉን ለምን የተጠበቀውን ያህል አላፋፋመም? ማድረግ የሚችለውን ያህልስ አድርጓል ወይ? ለሚሉት ጥያቄዎች እዚህ ላይ መልስ ለመስጠት አንሞክርም:: በተለዪ ለማቅረብ እንሞክራለን::
አንድ ነገር መጥቀስ ግን ያስፈልግ ይሆናል:: *"...በኅብረቱ አባላት መኻል ሊኖር በሚችለው አዝጋሚ የመተማመን ጉዞ አንዳንድ ያለቦታው መጠራጠር እየገባ ለሥራ መጓተትና አልፎ አልፎም ለመጠነኛ ግብታዊ አሠራር መጋለጥ ሊከሰት ይችላል.... የኅብረቱ ዋናና ተቀዳሚ እንቅፋት የምንሆነው የኅብረቱ አባላት እንደምንሆን መገንዘብ ያስፈልጋል... ከልክ ያለፈና ያላስፈላጊ እርስ በርስ መጠራጠር ቢያንስ ለአጭር ጊዜ ከባድ እንቅፋት እንደሚሆን.... የሚከሰቱ ልዩነቶች ሳይበግሩን ወይም የባሰ ሳያራርቁን የበለጠው የሕዝብ ዓላማና ጉዳይ ምንጊዜም እንዲቀድም ዕድል ከሰጠነው በወሬና በአሉባልታ ላለመፈታት ያለው ዕድል ሠፊ ነው.... በአጉልና መሠረት በሌለው ነገር ተጠራጥሮ ልዩነትን ማስፋት የሚጠቅመው አለመተባበራችንን ለሚፈልገው ክፍል ብቻ ነው ... ይኸ እንዲሆን የፈቀደ.... ምንም ባላሰበው መንገድ ቢሆን ለጠላት አገለገለ/ጠቀመ ማለት ነው .... ለኅብረቱ ሥራ እንቅፋት*

*የሚሆነው ሌላው ኅሉፋዊ (passive ) ትግል ማካሄድ ነው ....... "* ይኽን የወሰድነው ኅብረቱ በመጀመሪያ ሦስት ወራት ህልውናው ለመሥራት የተለመውን እቅድ ከዘረዘረበት "የአጭር ጊዜ የተግባር መርኃ ግብር" ብሎ ካወጣው ጽሑፍ ላይ ነው።

ያም ሆነ ይኽ አሁን ኅብረቱ ባለበት ደረጃ ማድረግ ያለበት ላይ ትኩረት ማድረጉ አግባብነት አለው።
በኅብረቱ ውስጥ ለተነሱ ጥያቄዎች በግልጽ ተወያይቶ መፍትሄ ለመስጠት፥ እየተባባሰ ከመጣው የአገራችን ሁኔታ አኳያና ቀኑ እየተቃረበ ላለው የሚቀጥለው ምርጫ ኅብረቱ እንደ ኅብረት አስቸኳይና በሁሉም ላይ በማያሻማ መንገድ ገዥነት ያላቸው ውሳኔዎችን መውሰድ ስለሚያስፈልግ ይኸንኑ በተመለከተ የኅብረቱ ሸንጎ ስብሰባ እንዲጠራ ለኅብረቱ ሁለት ደብዳቤዎችን መላካችን ይታወሳል።

## ፪. ቀጣዩን ምርጫ በተመለከተ

ኅብረቱ ሲመሠረትም ሆነ ከዚያም በኋላ ምርጫን በተመለከተ የበለጠ መብራራትና ግልጽ መሆን ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ የታወቀ ነው።
በኛ እምነት ኅብረቱ የሚቀጥለውን ምርጫ ለመወዳደር *መዘጋጀትና መሳተፍ* የሚኖርበት በተናጠል ድርጅቶች ሳይሆን *በጋራ ፕሮግራም* ላይ መሆን አለበት።
ይኽ እንግዲህ አንዱ በጉባዔው በሚገባ ግልጽ መሆን የነበረበትና ስምምነት ላይ ሊደረስበት የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ ነበር።
በመሆኑም አንዳንድ አባል ድርጅቶች "ያኔ በጉባዔው ያልተስማማንበትን እንዴት አሁን በጋራ ፕሮግራም እንወዳደር ይባላል?" የሚል አግባብነት ያለውና ሕጋዊ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ።
ኅብረቱ በኅብረት ደረጃም ይሁን አባል ድርጅቶች በጠቅላላው (ይኽ መቸም እስካሁን ከኅብረቱ ውጭ ያሉ ድርጅቶችንም የሚመለከት ይሆናል) አጥብቀው መጠየቅ ያለባቸውና ምላሽ ማግኘት (መስጠት) ያለባቸው ምርጫው ለምን ዓላማ ነው? ለሚለው ጥያቄ ይሆናል።
"አንድ ሰው አንድ ድምጽ" በሚለው መርኅ ሕዝብን የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን የሚያስችለውን ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ እውን ማድረጉ ሁላችንም የምንታገልለት ግብ ነው።
በአሁኑ ደረጃ ደግሞ ይኽ ግባችን በሥልጣን ላይ ያለውን ኃይል በሰላማዊ መንገድ የምንቀይርበት ዋና የመታገያ መሣሪያችንም ነው።
ስለዚህ ምርጫ የመታገያ መሣሪያችንም ግባችንም ነው ማለት ነው።
እንግዲህ የሚቀጥለው ምርጫ መታየት ያለበትና ኅብረቱም የሚዘጋጅበት የአገርና ሕዝብን ኅልውና ከማስጠበቅና ለዚሁና ለጠቅላላው እድገት፥ ለሰላምና ብልጽግና ጠር የሆነውን የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ከማስወገድ አኳያ ነው። ይኸን ደግሞ ማድረግ የሚቻለው በተናጠል ሳይሆን በጋራ በመቆምና በኅብረት በመታገል ብቻ ነው።
በኅብረቱ ስምምነትና እምነት ምርጫ የምናካሂደው አገራችንንና ሕዝባችንን ወደ አለመኖር እየወሰደ ያለውን ኃይል ከሥልጣን አስወግደን የጋራ ኅልውናችንን በማስከበር ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥቅም የሚሆን የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ሊወልድ የሚችል ሁኔታን ለማስገኘት ነው።
ስለዚህ አሁን ባለንበት የፖለቲካ አደረጃጀትና አቅም በተናጠል በመወዳደር ይኸንን የጋራ ዓላማ እውን አደርጋለሁ የሚል ድርጅት አለ? በኛ በኩል መልሱ በማያወላዳ መልኩ የለም ነው።
ይኽ እንግዲህ ያለውን ጠጣርና መራር ሃቅ በመገንዘብ ነው።
አስፈላጊውን ሁሉ መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁነቱ፥ ቁርጠኝነቱ፥ በጎ ፍላጎቱና ምኞቱ ያለን ብዙ ድርጅቶች አለን። ጥርጥር የለውም። ስሊታችን ግን በአገራችን ከአለው ውስብስብ ሁኔታና የፖለቲካ አደረጃጀታችንን በሚገባ ከማጤን አኳያ መሆን ይኖርበታል።

ያሻውን ለማድረግ ምንም ዓይነት የገንዘብ ችግር ከሌለበት የአገሪቱን ሃብትና ንብረት ጥቅልል አድርጎ ከያዘ የናጠጠ ሃብታም ነጋዴ መንግሥት፥ ይሉኝታ ቢስና በማጭበርበር ከተካነ ኃይል ጋር፥ በተለይ አሁን በእምቢተኛነት በተያያዘው እንደ አንድ ተወዳዳሪ ሳይሆን ተመራጭም፥ አስመራጭም፥ ተመልካችም፥ ዳኛም፥ አስፈጻሚም፥ ሁሉንም መሆን እንዲችል የምርጫውን ሂደት ከጅምሩ እስከ ድምዳሜው በብቸኝነት ሁለንተናዊ ቁጥጥር በሚያደርግበት ሁኔታ በተናጠል ተወዳድሬ በቁጥ ቁጥና፥ ጠ ብ ... ጠ ብ.. በሚል አካሄድ እርባና ያለውና ስሜት የሚሰጥ ለውጥ አመጣለሁ ማለት በአጭሩ አጉል ነው።

በተናጠል ድርጅት በምርጫ ለመሳተፍ የሚፈልግና የሚወስን የኅብረቱ አባል ድርጅት ካለ ከሁለት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ ተለውጧል ማለት ነው።

አንድም በኅብረቱ መሥራች ጉባዔ ላይ የተወሰዱት ግንዛቤዎች ስህተት ነበሩ፥ አልታመነባቸውም ወይም ደግሞ ለደረስንበትና ለወሰድነው የጋራ ግንዛቤ አቋም ያበቁን የአገሪቱ ሁኔታዎች ተለውጠዋል፥ ተሻሽለዋል፥ ከስመዋል ማለት ነው።

ታዲያስ የትኛው ነው የተቀየረው?

በተናጠል ድርጅት በምርጫ መሳተፍ ያሰቡና የወሰኑ ድርጅቶች ለነዚህ ግልጽ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋቸዋል፥ ይጠበቅባቸዋልም።

ሁላችንም እንደምናየውና እንደምናውቀው ደግሞ ከኅብረቱ መሥራች ጉባዔ ወዲህ የአገራችን ሁኔታ በመሻሻል ፋንታ የባሰ እየከፋ ነው የመጣው።

በነፃ ጋዜጠኞች ላይ፥ በተማሪዎች ላይ፥ ወዘተ... የሚደርሰው ወከባና ሽብር፥ በጋምቤላ ወገኖቻችን ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለው የዘር ማጥፋት ዘመቻ፥ ወዘተ.... የመሻሻልን ሳይሆን የሁኔታ መባባስን ነው የሚያሳዩት።

በእርግጥ ማንኛውም ድርጅት የሚመስለውን የፖለቲካ መሥመርና ስልት የመከተል ሙሉ ነፃነት አለው። ሆኖም ያ ድርጅታዊ ነፃነቱ የተሟላና አግቦ የሚኖረው ወዶ በሙሉ ፈቃደኝነት የገባውን ግዴታ መወጣት ሲችል፥ ቢያንስ አምኘበታለሁ፥ ተቀብየዋለሁ ያለውን የጋራ ግንዛቤ ለመተውና ለመሻር ያስቻሉትን በአገሪቱ ያሉ የሁኔታ ለውጦችን በሚያሳምን መልኩ ማስረዳት ሲችል ነው። ይኽ ደግሞ ከማንም ኃላፊነት ከሚሰማው ክፍል (ግለሰብም ይሁን ድርጅት) የሚጠበቅ ነው።

በእውነት መጠነ-ሠፊና ፈርጀ-ብዙ ለሆኑ ችግሮቻችን መሠረታዊና ዘለቄታዊ መፍትሔ ማስገኘት ግባችን ከሆነ ከአሁን በኋላ በአገራችን የሚደረግ ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ መሆንና በምንም መልኩ ያለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በያዘው ሁኔታ እንዲቀጥል የማያስችል መሆን ይኖርበታል።

አሁን ባለንበት አገዛዙ ከተቃዋሚው ለቀረበለት በጎ ሃሳብ ምንም ዓይነት አዎንታዊ ምላሽ በነፈገበት ሁኔታ ደግሞ በታሰበው ምርጫ በተናጠል መወዳደር በቀጥታ ያለውን መንግሥት በሥልጣን መቀጠል ያለጥርጥር የሚያረጋግጥና መርቆ የሚሰጥ ነው የሚሆነው።

የአገራችንና የሕዝቧ ህልውና መረጋገጥ ዓላማው ለሆነ፥ ለሰላምና መረጋጋት መኖር እንዲሁም ሥልጣን የሕዝብና ከሕዝብ ብቻ መሆኑን ለሚያምን፥ ከራሱ ይልቅ የአገርን ዘለቄታዊ ጥቅም ለሚያስቀድም ማንኛውም ድርጅት ያለው ምርጫ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ አገዛዙ በሚወስዳቸው የተለመዱ ሃላፊነት የጎደላቸው እርምጃዎች ሁኔታዎች እንዲከስሙ እስካልሆነ ድረስ፥ በጋራ ቆሞ በአንድ የጋራ ፕሮግራም በመወዳደር፤ ያለውን አገዛዝ ዕድሜ ማሳጠር ወይም በተናጠል በመወዳደር የአገዛዙን ዕድሜ ማራዘም ። ሌላ መንገድ የለም።

አንዳንድ ድርጅቶች አይ በጋራም ሆነ በተናጠል አንወዳደርም ስለዚህ ይህ እርምጃችን ያለው አገዛዝ በሥልጣን መቀጠል አለመቀጠሉ ላይ ምንም ጫና የለውም ሊሉ ይችላሉ። ይኸም ልክ አይመስለንም። በምርጫ መሳተፍም ይሁን በሆነ ምክንያት አለመሳተፍ ካለ እሱም ቢሆን የጋራ አቋም መሆኑ ተገቢ ነው እንላለን።

የአቶ መለሰ አገዛዝ ከአገር ዘለቄታዊ ጥቅም፥ ሰላምና መረጋጋት ይልቅ ሥልጣንን የሙጥኝ ማለት ልማዱ ስለሆነ በዚህ ቀጣይ ምርጫ ብቻውን ከራሱ ጋር ተወዳደረ እንዳይባልና የተወሰነ "ሕጋዊነት"ና በተለይም በውጭው ዓለም ዘንድ "ተቀባይነት" ለማግኘት ወይም ነቀፌታን ለማለዘብ ሲል የሚያጅቡት ድርጅቶችን ማሰለፉ የሚጠበቅ ነው።

በአለን መረጃም እሱ ለመደባቸው ወይም ፈቃደኛ ተባባሪ ለሆኑ ድርጅቶች ከጠቅላላው እስከ ሰላሳ እጅ (30 %) መቀመጫ ለመተው አስልቶ ተቀምጧል::

በዚህ አካሄድም በአገሪቱ ምንም ዓይነት አዎንታዊ ለውጥ እንዳይኖር ለማረጋገጥ ምን ያህል እንደተዘጋጀ ያሳያል::

እንግዲህ በምርጫው ሂደት በተናጠል እንሳተፋለን የሚል ሃሳብ ያላቸው ድርጅቶች የሚያከናውኑት ይኸን የነ አቶ መለስ ዜናዊን ምኞት እውን ማድረግ ብቻ ነው ማለት ነው::

ግንዛቤ የሚያስፈልገው አንድ ድርጅት በራሱ የግል ፈቃድና ፍላጎት በሚቀጥለው ምርጫ ተወዳድሮ የፈለገውን ያህል መቀመጫ ቢያገኝ ቢበዛ እስካሁን በብዙ መስዋእትነት በተመሳሳይ ሁኔታ በፓርላማው መቀመጫ አግኝተው የሚቻላቸውን ሁሉ ለማድረግ ከሞከሩት ወገኖች የተለየ ምንም ማድረግ ፈጽሞ አይቻለውም::

ሁሉም እንደሚያውቀው አገሪቱ ደግሞ በአዝጋሚ አካሄድና በአገዛዙ በጎ ፈቃድ የሚፈታ ቀላልና አዝናኝ ሁኔታ ውስጥ አይደለም ያለችው::

እንደ እውነቱ ከሆነ የኅብረቱ መሥራች ጉባዔ የአገራችንን ሁኔታ ሲገመግም በደረሰበት የጋራ ግንዛቤ መሠረት ዘግናኝ፥ አሳፋሪና አስቸኳይ የጋራ ምላሽን መስጠት ከሚያስፈልግበት ሁኔታ ላይ ትገኛለች:: ይኸም ማለት በአጭሩ አገራችን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን የሚያሳውጅ ኅልውናዋን አጥብቆ ከሚፈታተን አደገኛና ከባድ የችግር ሁኔታ ላይ ነው የምትገኘው ማለት ነው::

የአገራችን ሁኔታ በዚህ ደረጃ ላይ ካለና ይኸንን ከተቀበልን ደግሞ አስተሳሰባችን፥ አሠራራችንና ምላሻችን መጣኝ መሆን ይኖርበታል:: ይኸ በተግባር ሲገለፅ ደግሞ አንዳንድ የየግል ድርጅት ጥቅሞችን ወይም አቋሞችን በይደር መያዝ እንገደዳለን ማለት ነው::

በሌላ በኩል ተቃዋሚው በምርጫ መሳተፍ ያለበት በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ የጠየቅናቸውን ለነፃና ርቱአዊ ምርጫ የሚያበቁ ሁኔታዎችን ለማሟላት ሙሉ በሙሉ ሲቀበልና በእርግጥ በተግባር ሲያስመሰክር ብቻ ነው፤ ይኸን ካላደረገ በምንም መልኩ በምርጫ አንሳተፍም የሚሉ ወገኖች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው::

ይኸ ከባድ የግንዛቤ ግድፈት ይመስለናል:: ግልጽ እንሁን:: ሥልጣንን ከግል ኅልውናው ጋር አያይዞና ከሱም አኳያ ብቻ የሚያይ፥ የአገር ሰላምና መረጋጋትም ይሁን ብሔራዊ አንድነትና ዘለቄታዊ የወገን ብልጽግና እንግዳ የሚሆንባቸው የነ አቶ መለስ አገዛዝ ቀርቶ መኻከለኛ ዴሞክራሲያዊ ዝንባሌ አላቸው የሚባሉ ክፍሎችም ቢሆኑ ተቃዋሚው ሌጣ ጥያቄ ስላቀረበ ብቻ ሁኔታዎችን ለተቃዋሚው በሚያመች መልክ አሟልቶና አደላድሎ ይሰጣል፥ በመሶበ ወርቅ ያቀርባል የሚል አመለካከት ሲበዛ ምኞታዊና በጣምም ግብዝነት፥ ይኸን ለማሳመን የሚቀርብም ማንኛውም ምክንያት በጣም የሳሳና የሰለለ ይሆናል::

ኅብረቱም ላቀረበው የሁኔታዎች መሟላት ጥያቄ አመርቂና የሚያሠራ መልስ የሚያገኘው ጥያቄውን አስገዳጅነት ባላቸው መንገዶች ሲያጅብ ብቻ ነው:: እነኝህም መንገዶችና ዘዴዎች የትግል ዘርፎች ናቸው:: የተጠየቁ ጥያቄዎች መሟላትና አለመሟላታቸውን የምንለካው አገዛዙን እባክህ አሟላልን በሚል ልመናም ይሁን ከወዲሁ ይኸን ካላደረክ የፖለቲካው ጨዋታ አልቆለታል የሚል አካሄድን በመከተል አይደለም:: በሂደቱ ውስጥ በመሆን ብቻ ነው አንድ ነገር መሥራት አለመሥራቱን ወይም ማስኬድ መቻሉም ሆነ አለመቻሉን ማወቅ የሚቻለው::

ስለሆነም የኅብረቱ አካሄድ ሕሊናዊም ይሁን እንቅስቃሴአዊ ዝግጅታችን በምርጫው እንደምንሳተፍ መሆን ይኖርበታል::

ስለዚህ በቀጣዩ ምርጫ ለመሳተፍም ሆነ ላለመሳተፍ የሚያስወስነን አገዛዙ የሚሰጠውን ምላሽ ብቻ በነጠላው በማየት ወይም በመጠበቅ ሳይሆን እኛ (ኅብረቱ) ለሁኔታዎቹ መሟላት ምን ያህል ጠንካራ እንቅስቃሴ ማድረግ መቻላችን ነው ዋናው:: አገዛዙ የፖለቲካውን ማእከል መዝጊያ ነው ክርችምና ጥርቅም አድርጎ የዘጋው፤ በሩን ዘግቶ ቁልፉን ጥሎታል:: አሁን ቁልፉ እኛው ጋ ነው ያለው:: ያም ቁልፍ የተባበረ የጋራ ትግል ነው፤ የሕዝብ ትግል:: ተመልሶ እንዲጠፋ (እንዲከስም) ዕድል አንስጠው ነው የምንለው::

በቀጣዩ ምርጫ የየድርጅታችንን የፖለቲካ ፕሮግራም ለጊዜው በይደር ይዘን በኅብረቱ ደረጃ በጋራ ለመወዳደር የምንገደደውም ከላይ በተጠቀሰው እጅግ አሳሳቢ ከሆነው አገራዊ ሁኔታ አንጻር፥ ከአለው የአደረጃጀትና የፖለቲካ አቅማችን አኳያ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

ይኸ መቸም አንጻራዊ በሆነ መልኩ በአገዛዙ ሕጋዊነት ከተነፈጋቸው የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ይልቅ በተለይ በአገር ውስጥ ሕጋዊነት ኖሯቸው ከሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በኩል የበለጠ ድርጅታዊ መስዋዕትነትን ይጠይቃል። ለጋራ ትግል ሲባል ሕጋዊነት የተነፈጋቸው አንዳንድ አባል ድርጅቶች የሚከተሉትን የትግል መሥመርና ስልት ለመተው እንደተገደዱት ማለት ነው። በሁለቱም በኩል የሚከፈለው መስዋዕትነት ለጋራ ጥቅምና ለጋራ ችግሮቻችን ዘለቄታዊ መፍትሔን ከማፈላለግ አኳያ ነው።

የጋራ ሥራ ደግሞ መሠረቱ መቻቻል ስለሆነ ለጋራ ጥቅም ሲባል አንዳንድ በየግላችን የያዝናቸውን አቋሞችና መሥመሮች በይደር መያዝን፥ ማጣጣምን፥ ማዋዋጥንና ሲያስፈልግም መተውን ይጠይቃል። የጋራ ሥራ የሚሠምረው ደግሞ እንደዚህ ያለ መስዋእትነትን መክፈል ሲቻል ብቻ ነው።

ስለሆነም የሚቀጥለው ምርጫ ላይ በጋራ ተወዳድረን የምንፈልገውን ውጤት ማስገኘት እንችል ዘንድ አባል ድርጅቶች በግል የፖለቲካ ፕሮግራማቸው አለመወዳደራቸው ይበጃል ማለት ነው።

በተናጠል የድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራምን ይዞ የሚደረግን የምርጫ ውድድር ኅብረቱ በበላይ የማቀናጀትና የማስተባበር አካሄድን ጉድለትና ጥቅመ-ቢስነት በተመለከተ፥ እንዲሁም በጋራ መድረክ በምርጫ ለመሳተፍ ምን ዓይነት ዝግጅትና አካሄድ እንደሚያስፈልገን በመኢሶን ወንድሞቻችን የቀረበውን ትንታኔ ሙሉ በሙሉ ስለምንቀበለው እዚህ ላይ በድጋሜ ማቅረቡ አስፈላጊ አይሆንም።

<u>ለሁላችንም ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ማንም ድርጅት ምንም ያህል በጎ ፈቃድ ቢኖረው ብቻውን ወይም ሁለትና ሦስት ሆኖ በምርጫ በማቸነፍ የሚፈለገውን የአገር ደኅንነትና አንድነት ማስገኘት/ማምጣት እንደማይቻል ነው። አሁን አገራችን በምትገኝበት የተወሳሰበ ሁኔታ ሰላም፥ መረጋጋት፥ የአገር አንድነት፥ደኅንነትና ፀጥታ ሊረጋገጡ የሚችሉት ብሔራዊ መግባባትን (**National Consensus**) የሚያስገኝ ሁኔታ ማምጣት ሲቻል ብቻ</u> ነው።

በሚያሳዝን መልኩ አሁን በአለን ይዞታና አደረጃጀት ደግሞ ማንም ድርጅት በሚያደርገው የተናጠል እርምጃ/ትግል ብሔራዊ መግባባትን የሚያሰፍን ሁኔታ ማስገኘት አይችልም።

ብሔራዊ መግባባት ላይ የተመሠረተ መረጋጋትና ሰላም በሌሉበት ሁኔታ ደግሞ ወደ ተሻለ የሥርዓት ለውጥ መሸጋገር የማይሆን ጉዳይ ነው።

እንኳን በጠቅላላ የፖለቲካ ይዞታችን ኅብረቱ ከተፈጠረ በኋላ እንኳ በኅብረቱ አባል ድርጅቶች መኻል ሳይቀር የሚታየው ተቻችሎ የመሥራትና ለትልቁ የአገር ዓላማ የግል ድርጅት ዓላማን የማስገዛት ባህሪ መጉደል፥ የትግሉ ቅደም ተከተል ተዘባርቆብን ብዙ ወርቃማ የትግል ጊዜን በአተካሮና በእርስ በርስ መናቆር ማባከን፥ ወዘተ... አንድ ድርጅት ወይም ሁለት ሦስት ሆኖ መሠረታዊ ለውጥ ማስገኘት የሚችል ሁኔታን ማምጣት ላለመቻሉ ገሃድ ማረጋገጫ ነው።

እዚህ ላይ መገንዘብ ጥሩ የሚመስለን ይኸ የሆነው የግድ ያሉት ድርጅቶች ወይም መሪዎቻቸው የማይረቡ ሆነው ወይም አገር ሰላም እንዳትሆን ሆን ብለው ስለሚተናኮሉ አይደለም። በጣም በአብላጫው ባለፉት ሰላሣ ዓመታት ያሳለፍነው ጠመዝማዛ የፖለቲካ መንገድና በተለይም ባለፉት አሥራ ሦስት ዓመታት የሕወሓት/ኢሕአዴግ ኋላ-ቀር አገዛዝ የወለደውና የወጠረን ውጥንቅጥ የፖለቲካ ሁኔታ የወለደውና ያተረፈልን ጉድ ነው።

በተናጠል ተወዳድሬ፥ የተንፏቀቀም እንኳ ቢሆን፥ በአዝጋሚና ኅሉፋዊ አካሄድ ለውጥ አስገኛለሁ የሚለው ቀቢፀ-ተስፋ የአገርንና የጋራ ጥቅምን በበቂ ያላገናዘበ፥ የችግሮቻችንን መጠን፥ ስፋትና ጥልቀት ያላጤነ እንዲሁም የወገንን ችግር ከምርና ከልብ ያላመነ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል።

በኅብረሕዝብ በኩል በተናጠል በሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ትግል በአገራችን ላለው የተዘበራረቀና እየከፋ ያለ ሁኔታ አዎንታዊና የአብዛኛውን አመኔታ የሚያስገኝ የሥርዓት ለውጥ ማስገኘት አይችልም የሚለው እምነታችን የጠና ነው።
በተናጠል ጉዞ ከተሄደ ምናልባት ከበጎ ፈቃድና ከመልካም ኢትዮጵያዊ ምኞት ውጭ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ካደረገውና ከሚያደርገው የተለየ ማድረግ የሚቻል አይሆንም።
በተናጠል ትግሉን (ምርጫም ይሁን ሌላ) ለመቀጠል ማሰብና ማድረግ ትርፉ አንድም አቅም ኖሮ በመሣሪያ ኃይልና በጉልበት የሚመጣ ወታደራዊ አምባ ገነን አገዛዝን መጋበዝ አለያም አሁን በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ በጥፋት ጉዞው እንዲቀጥል አጃቢ መሆን ነው። በሌላ አባባል አገሪቱን ወደ ጥፋት እየወሰደ ላለው የአቶ መለሰ መንግሥት በሥልጣን የመቆያ ዋስትና መሆን ማለት ነው። ይኽ ደግሞ ሁላችንም የምንመኘውንና የምንታገልለትን መልካምና የተሻለ የሥርዓት ለውጥ አለማስገኘት ብቻ አይደለም የጋራ ኅልውናችን ላይ ጨክኖ መፍረድ ማለት ነው።

እንደሚታወቀው ምርጫ የሚካሄደው ምርጫን ለማካሄድ ያህል ወይም ለይስሙላ ምርጫ ተካሂዷል ለማለት አይደለም።
ምርጫ የሚደረገው የሥልጣኑ ባለቤት የሆነው ሕዝብ በበጎና ነፃ ፈቃዱ የሚሻውንና የሚፈቅደውን ግለሰብም ይሁን ድርጅት ለተወሰነ ኃላፊነት ለተወሰነ ጊዜ መሰየም እንዲችል ነው።
ለአንድ አገር መረጋጋት፥ ሰላምና ብልጽግና ደግሞ ነፃና ፍትኃዊ ምርጫ ማካሄድና በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት የተቋቋመ ሥርዓት እጅግ አስፈላጊ ናቸው።
በአገራችን ግን እስካሁን እንደታየው፥ ምንም እንኳ አጋጣሚዎች ሳይኖሩ ቀርተው ባይሆንም፥ እነኝህ እውን አልሆኑም። በመሆኑም ችግሮቻችን ከመባባስ በስተቀር አልተወገዱም።
አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጩ ፖሊሲዎችን በስሊት ሆን ብሎ የሚከተልና መሠረታዊ ለሆኑ መብቶች እንኳ ደንታ-ቢስ የሆነ፥ አልፎም የአንድ ሰው ፍጹም አምባ ገነንነትን እያጠናከረ ያለ አገዛዝ እስካለ ድረስ የባሰ ወደ ከፋ ችግር እየተጓዝን መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም።
ስለ አሉን ችግሮች፥ ችግሮቻችንን በሰላም ለመፍታት ስላመለጡን መልካም ዕድሎችም ሆነ ዕድሎቹን ስላከሰሙብን የሕዝብን ጥቅም የተጻረሩ ኃይሎች ያለን ትረካ አሁኑኑ ማክተም ይኖርበታል።
አሁን በዚህ ታሪካዊ ወቅት በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ላይ የምንገኝ ድርጅቶች መሠረታዊ የሆነ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ አድርገን ለአንዴና ለመጨረሻ የዛሬው ሳይሆን የነገው ታይቶን፥ ለእኛ ሳይሆን ለዚያ ግልቱ ሆኖም ግን ኩሩ ሕዝብ፥ ለዛች "ያልታደለች" ሆኖም ግን ባለ ታሪክ አገር፥ ለአሁኑ ሳይሆን ለነገውና ከዚያም ለሚቀጥሉ ትውልዶች የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ዛሬ መሠረቱን እንጣል። ይኽ ማለት ደግሞ ነገሮችን ከየራሳችንም ይሁን ከየድርጅቶቻችን አኳያ ብቻ ሳይሆን ከጠቅላላችንና ከዘለቄታዊ የጋራ ጥቅማችን አኳያ አይተን እንሥራ ማለት ነው።
<u>በኛ እምነት ለአገራችንና ለዝንትዓለም ሰቆቃ ለተዳረገው ወገናችን መሠረታዊ ለውጥ ለማስገኘት ያለን ዕድል ኅብረቱ በኅብረት ደረጃ በቀጣዩ ምርጫ ሂደት ለመሳተፍ ሲዘጋጅና ሲችል ወይም ይህንን በተመለከተ የጋራ የሆነ የትግል አቋም ሲይዝና ሲከተል ብቻ ነው።</u>

አንዳንድ ወገኖች የምርጫው ጊዜ ስለተቃረበ በኅብረቱ ደረጃ ለውድድር ለመቅረብ በቂ የመዘጋጃ ገዜ የለም፥ መንግሥትም ኅብረቱን በኅብረት ደረጃ ተመዝግቦ እንዲወዳደር አይፈቅድም፥ ይኼ ከሆነ ደግሞ አንዳንድ ድርጅቶች ባላቸው አቅም በተናጠል የሚኖራቸውን ዕድል መንፈግ እንዲያውም ማበላሸት ይሆናል የሚሉ እንዳሉ ግልጽ ነው።
አባባሉ እውነታን የተመረኮዘ ነው። ሆኖም መሠረታዊ የአመለካከት ፍልሰት ያለው ይመስለናል።
የያዝነው ትግል ነው። ማንም ትግል ደግሞ ግብ የሚመታው የትግል አጀንዳውን እለውጠዋለሁ የሚለው አካል (መንግሥትም ይሁን ድርጅት) ሙሉ በሙሉ

እንዲቆጣጠርበት እስካልፈቀደ ድረስና የተሟዘዘ የተከላካይነት ጠባይ ያጠቃው የዛመሞ ትግልን እስካልተከተለ ድረስ ብቻ ነው።

በመሆኑም ይኽን ምርጫ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በፈለገው መንገድና እንዳሻው የሚያካሂደው ከሆነ፥ የተሻለ ለውጥ እናመጣለን የምንለው የተቃዋሚው ክፍል ሙሉ በሙሉ የሚለውን ከተከተልንና የሚፈልገውን ከፈጸምን እንዴት ነው ለውጥ የሚመጣው? ይኽ ከሆነ ደግሞ ተቃዋሚው ከአገዛዙ ግልጽ የሆነ የአቋምና የአስተሳሰብ ልዩነት የለውም ማለት ነው። ትግሉስ የት ላይ ነው? የዚህን ዓይነት አካሄድ ለመከተል መሰባሰቡስ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? በሥልጣን ላይ ያለውስ ኃይል ምን አስገዳጅ ነገር ኖሮበት ነው የምንፈልገውን ለውጥ እኛ ስለፈለግነው ብቻ ለማስገኘት ቀርቶ ለማስተናገድ የሚሻው? ከሞቀ አገር የማፍረሻ ወንበሩ ለምን ይነሳል ብለን እናስባለን? ወይስ ለእነ አቶ መለስ በሆነ ተአምር በጎው ይገለጽላቸዋል ብለን እናስባለን ማለት ነው?

የተቃዋሚው ወገን ተግባር መንግሥት በሚለውና በሚፈልገው "እራሱን አርሞና አስተካክሎ" ለመታዘዝ ራሱን ማዘጋጀት አይደለም። የለውጥ ፈላጊው ክፍል ኃላፊነት ሲቻል ተቃዋሚው የሚለውን መንግሥት እንዲቀበል ማስገደድ ቢያንስ ግን መኻል መንገድ ለመገኛኘት መታገልና ማስቻል ነው።

ስለዚህ የሚቀጥለው ምርጫ እንዲካሄድ ኅብረቱ ያቀረባቸውን ሃሳቦች መንግሥት ተቀብሎ ተግባራዊ እንዲያደርግ ሕይዎት ያለውና የተጧጧፈ ትግል ማድረግ ይኖርብናል። ቀደም ሲል በመኢሶን ከቀረቡት ሃሳቦች በተጨማሪ ይኽ እንዴት መከናወን እንዳለበትና እንደሚቻል በተለይ እናቀርባለን።

አንዱ ጥያቄ የሚሆነው እንግዴህ ኅብረቱ በኅብረት ደርጃ ተመዝግቦ እንዲወዳደር ማስቻል ነው።

የጊዜውም ጉዳይ እንዲሁ ነው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የምርጫውን የጊዜ ሰሌዳም ለማስለወጥ መታገል ይኖራል።

ምርጫውን በተገቢ ለማካሄድ ያቀረብናቸውን ሃሳቦች መንግሥት እንዲቀበል ለማድረግ፥ ኅብረቱን በኅብረት ደረጃ እንዲወዳደር ለማስመዝገብም ሆነ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የምርጫውን ጊዜ ለማስለወጥ ጭምር እንዲሁም እንደተለመደው ሁሉንም አሻፈረኝ ካለ በምርጫ መሳተፍን ትቶ ሌሎች አማራጮችን ለማየት የሁላችንም የጋራ አቋም መሆን ሲችል ብቻ ነው አዎንታዊ ውጤት የሚገኘው። ከዚህ የጋራ አካሄድ የተለየ የተናጠል መንገድ መከተል ለአገርም፥ ለወገንም እንዲሁም ለማንም ድርጅት ጠቃሚ ሲሆን አይታየንም።

እንግዲህ ይኽ አንደኛውና የመጀመሪያው መንደርደሪያ የትግል አካሄዳችን ነው።

ኅብረቱ በኅብረት ደረጃ ማለትም በአንድ የጋራ ፕሮግራም በምርጫ መወዳደሩ ብቻ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ለማስወገድ ከመቻል ወዲያ የምንለውን ዘለቄታዊ ለውጥ አያመጣም።

በሥልጣን ላይ ያለውን ክፍል ካለበት ማውረድ የሚያስፈልገው ደግሞ በእሱነቱ ወይም ከሥልጣን ለማስወገድ ያኽል ብቻ ሲባል አይደለም፥ መሆንም የለበትም። እሱ ሊያስገኝልን ብቃቱም ሆነ በጎ ፈቃዱ የሌለውን ለሁሉም፥ ለእሱም ጭምር፥ የሚሆን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት እንጅ።

## ፫. ድኅረ-ኢሕአደግ

ኅብረቱ ከላይ እንደተጠቀሰው የሕወሓት/ኢሕአዴግን መንግሥት በምርጫ ሂደት በመሳተፍ ወይም በሕዝብ የተባበረ ትግል በሰላማዊ መንገድ ከሥልጣን ካስወገደ በኋላ፥ ከመሠረታዊ የአገርና የወገን በጎ ዓላማችን አኳያ፥ በምን ዓይነት መንግሥት መተካት እንዳለበት ከወዲሁ መስማማት መቻል የጠራ የትግል መሥመር እንዲኖረንና ይኽንን የጋራ ትልም በመከተልም በአንድ ልብ በጋራ ለመንቀሳቀስ እንድንችል ይረዳናል፥ ይጠቅማል፥ ያስፈልጋልም እንላለን።

ይኸ ሁለተኛው የትግል ምዕራፍ ከመጀመሪያው ክፍል የበለጠ ድርጅታዊና የግልም መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ነው::
ከአባል ድርጅቶችና ከመሪዎቹ በመጀመሪያው ምዕራፍ እንደሚጠየቀውና እንደሚጠበቀው እዚህም ላይ የዘለቄታውን የጋራ ጥቅም ማስቀደምና ለጋራ ዓላማ ተገዥ የመሆን አርቆ አስተዋይነትና ታጋሽነትን፥ የበለጠ መቻቻልን፥ ቁርጠኝነትንና ድፍረትን አበክሮ ይጠይቃል::
ይኸ በእውነቱ በተለይ በየድርጅቱ አመራርና ሃላፊነት ላይ ለምንገኝ ግለሰቦችም ይሁን ለእያንዳንዱ ድርጅት ትልቅ ፈተና ነው:: ጥያቄው ፈተናውን ለማለፍ ስንቶቻችን ዝግጁ ነን? የሚለው ነው:: በኛ በኩል በሁሉም ድርጅቶችና ሃላፊዎች ላይ ያለን እምነት ከፍተኛ ነው::
ከሦስት እስከ ሠላሳ ዓመታት በላይ ለሚሆን ጊዜ ለተሻለ ሥርዓት የታገሉና በመታገል ላይ ያሉ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ለዚህ ወሳኝ ሽግግር የተወሰነ መስዋእትነት ለተወሰነ ጊዜ አያደርጉም የሚል ጥርጣሬ የለንም::
እንደ እውነቱ ከሆነ ይኸን ማድረግ ካቃተንና ካዳገተን ለአገሪቱና ለሕዝቧ የምንሰጠው አማራጭ እጅጉን የከፋ ነው:: ከዚህ አኳያ ቅድሚያ በየራሳችን ላይ መሠረታዊ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ አድርገን ትግሉን በአዲስ መንፈስና ዝግጅት ካልቀጠልን የታገልንበትና የምንታገልለት የሕዝብ ዓላማም ከንቱ የመሆን ዕድሉ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ አሁን ሰፊ እንደሚሆን መገንዘቡ መልካም ይመስለናል::
የኅብረቱ አባል ድርጅቶች በቀጣዩ ምርጫ በአንድ የጋራ ፕሮግራም በኅብረት ደረጃ በመሳተፍ ወይም ይህ እንዳይሆን አገዛዙ ሁኔታዎችን ካወናገረ ቀጣይነት ባለው ሕዝብን በስፋት ባሳተፈ የጋራ እርምጃ ያለውን አገዛዝ ከሥልጣን ለማስወገድ ይችላሉ የሚል የጠና እምነት አለን::
ከወዲሁ ሙሉ መግባባት ሊኖርና በግልጽ መወሰንና መዘጋጀት የሚያስፈልገው ከዚያስ በኋላ የሚተካው መንግሥት ምን ዓይነት መንግሥት ነው? የሚለው ዐቢይ ጉዳይ ይሆናል::
ኅብረቱ በኅብረት ደረጃ በምርጫ ተሳትፎ በአቸናፊነት ሲወጣ መቋቋም ያለበት ቀጣዩ መንግሥት በኅብረቱ አባል ድርጅቶች የሚቋቋም የጥምር መንግሥት መሆን እንዳለበት የሚያምኑ ድርጅቶች ይኖራሉ::
በኛ በኩል ይኸ አካሄድ ችግር ያለውና ለአፈጻጸም ቢያንስ አስቸጋሪ ሆኖ አግኝተነዋል:: አሁን ባለው ሁኔታ ምንም እንኳ ለምርጫ የሚደረገው አካሄድ በኅብረት መሆኑ አማራጭ የሌለው ቢሆንም በተገቢ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚያሻው ጉዳይ በምርጫውም ሆነ ከምርጫው በኋላ የሚሠራበት አሁን ያለው ለማሻሻል ተስፋ የሌለው ቀያጅ ሕገ-መንግሥት በመሆኑ በምርጫው ድል ያደረገው የተቃዋሚው ክፍል በተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) ባለው የበላይነት ጠቅላይ ሚኒስትሩን መሾምና ይኸም ሰው መንግሥቱን የማቋቋም ሂደትን ነው የሚከተለው:: ያለውን ሕገ-መንግሥት እንደሆነ በእሱው እየሠሩ እንዲሁ በቀላሉ ለማሻሻል እንደማይቻል ግልጽ ነው:: በአለው ሕግ በምርጫ የተሰየመውና በዚሁ ሕግ መሥራት የሚገደደው ፓርላማም ሕገ-መንግሥቱን ለመቀየር የሕገ-መንግሥቱ አፈጣጠርና አሠራር ሆን ተብሎ የተጠላለፈ በመሆኑ "ሕጋዊ " ኃይል አይኖረውም::

ድርጅቶች በመኻላቸው ያለውን አለመተማመንና መጠራጠርን ገና ማስወገድ ቀርቶ በአጥጋቢ አላረገቡትም:: ሁላችንም በሚደረገው ምርጫ ሁሉም ድርጅቶች ገብተው በምርጫው መሳተፍ አለባቸው ብለን እናምናለን፤ ለዚሁም ኅብረቱ እየታገለ ነው:: ምርጫው ማንንም ያላገለለና ሁሉንም የሚያሳትፍ እንዲሆን ደግሞ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ማንኛውም ሃላፊነት የሚሰማውና የመድብለ ፓርቲን ሥርዓት የሚቀበል የፖለቲካ ኃይል ሊታገልለት የሚገባ ዓላማ ነው::
በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች መግባትና መሳተፍ እንኳ ባይችሉ ተሳትፎአችን በኅብረት ደረጃ እንደ ኅብረት መሆን ስላለበት ሁሉም እንደተሳተፉ ሊቆጠር የሚቻልበት ሁኔታ አለ፡፡ ሆኖም ግን በምርጫው በአካል የተሳተፉና በአካል ተገኝተው መሳተፍ ያልቻሉ አባል ድርጅቶች በጋራ የጥምር መንግሥት የማቋቋሙ አሳብ በተለይ በአለን ይዞታና ሁኔታችን በጣም አስቸጋሪ ነው:: በመሆኑም የተሻለ ሰላማዊ ሽግግር

ማድረግ የሚቻልበት ወርቃማ ወቅት ባልታሰበ መጠላለፍና ሽኩቻ፥ በአልሆነ ንትርክና አጉል አተካራ የመክሰም ዕድሉ ጎላ ይላል ማለት ነው። ይኸ ደግሞ ይቅርታ የማይደረግለት በሕዝብ ተስፋ ላይ የሚፈጸም በደል ይሆናል።
እውነተኛ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ በሚነሳበት ሁኔታ ቀርቶ ወደ ሥልጣን የሚወስደው መንገድ ላይ ያለውን የጋራ እንቅፋት ለማስወገድ በምናደርገው ትግል የገጠመንን ተጨባጭ ችግር እያየነውና እየኖርነው ያለ ሃቅ ነው። ይኸ መቸም የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ቢሆንም መራር ሃቅ ስለሆነ ነው ለማስገንዘብ ያህል የጠቀስነው።
የሁሉም የጋራ ባላንጣ የሆነ አገር አጥፊ ቡድን እያለ በጋራ ለመሥራት ችግር ባለበት በዚህ ሁኔታ ያለውን መንግሥት ከስልጣን አውርደን በጋራ የጥምር መንግሥት ማቋቋም ይሻላል/ይቻላል ማለት አገሪቱን የውዝግብ አውድማ እናድርግ ከማለት አይዘልም።
ይኸን የምንለው አሁንም ከድርጅቶች ተፈጥሮ ባህሪ፥ ከነብረቱ የእድገት ደረጃና ድርጅቶቹ ከምናደርገው፥ ካለንበትና ከምናየው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ነው።

የጥምር መንግሥት የተሻለ የመሥራት ዕድል የሚኖረው የመታገያው መድረክ ለሁሉም በእኩል ሲመጣጠን ወይም በተመሳሳይ እይታና መንገድ ለታገሉ ፥ ለምሳሌ እንደወያኔ፥ ኦነግ፥ ወዘተ... በመሣሪያ ኃይል "ለውጥ" ላመጣ ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አደረጃጀት በእኛ አገር ያለው ዓይነት ውጥንቅጥ ሳይሆን ከሞላ ጎደል አንድ ወጥ ሆኖ ሲገኝና ቢያንስ መቆሚያ መሠረቱ ላይ ተመሳሳይ እይታ ሲኖር፥ ለምሳሌ እንደ ኬንያ ሲሆን ነው። በዚህ እውነታ ላይ ለሚገኙና ለውጥ ለማምጣት ለሚታገሉ ድርጅቶች የእያንዳንዱን የሥልጣን ድርሻ በቅድሚያ ለመወሰን ሁኔታው የተሻለና የቀለለ ይሆናል።
እስኪ ለማወዳደር ይረዳ ዘንድ እዚህ በምሳሌነት የጠቀስነውን የኬንያውን ሁኔታ ከኛ ጋር እናስተያየው፤

1. ለረዥም ጊዜ በኬንያ ብቸኛ የሥልጣን ባለቤት የነበረውን በቀድሞው የኬንያ ፕሬዘደንት አቶ ዳንኤል አራፕ ሞይ የሚመራውን የካኑ ፓርቲ ከሥልጣን ለማስወገድ የተባበሩት አሥራ ስድስት የፖለቲካ ድርጅቶችን ይዞታ በምናይበት ጊዜ የፖለቲካ እምነታቸውና ለአገራቸው ያላቸው ራዕይ እንደ ቁጥራቸው ይብዛና ይለያይ እንጅ በአንድ መሠረታዊ ነገር ሁሉም አንድ ነበሩ። አንዳቸውም ድርጅታቸው የቆመበትን ክፍል ከአገራቸው ከኬንያ "ነጻ" ለማውጣት ወይም ከሌላው ተለይቶ ለመኖር የቆመ አልነበረም። አንዳቸውም ኬንያዊነት ላይ ጥያቄ አልነበራቸውም። ትግላቸው በጥቅሉ በተወሰደ የወል " ልዩነታቸው" ላይ ያተኮረ አልነበረም። ሁሉም የቆሙትና የታገሉት ለጋራ እድገታቸውና ብልጽግናቸው እንቅፋት ሆኖ የታያቸውን መንግሥት በተሻለ ሥርዓት ለመለወጥ ነበር። በመሆኑም በአንድ የጋራ መድረክ መታገል ብቻ ሳይሆን እሱን አስወግደው የጥምር መንግሥት ለማቋቋም አንጻራዊ በሆነ መልኩ ቀለል ያለና የተሻለ የአደረጃጀት ይዞታና ሁኔታ ላይ ነበሩ።
2. ኬንያን ከእንግሊዝ ቅኝ ተገዥነት በታኅሣሥ 12 ቀን 1963 ዓ/ም (እ.አ.አ.) ነፃ ለማውጣት ከቻለው ሕዝባዊ የአመጽ እንቅስቃሴ በኃላ የተፈጠሩ በአገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ላይ ሚና ያላቸው ድርጅቶች አደረጃጀታቸው፥ ድርጅታዊ ይዞታቸውና የተከተሉት የትግል ስልት አንድ ዓይነት የሰላማዊ ትግል ብቻ እንጅ ከዚያ የተለየ አለመሆኑም ሆነ እንደኛ አገር በልዩ ልዩ ቀለማት ባሸበረቁ ግብ ግቦችና ትንንቆች የመተላለቅ አሳዛኝ ሂደትና ሰቀቃ ውስጥ አለማለፋቸው በመኻላቸው የተወሰነ ሥነ ልቦናዊ የፖለቲካ ቅርርብና መተማመን እንደሚኖር እረድቷል ማለት ይቻላል። ይኸም በእኛ ዘንድ እስካሁን የመፈታት ዕድል ካላገኘው የታመቀ የውስጥ ቂምና መጠራጠር ጥንውት የተላቀቁ ስለሆነ እነሱ የተሻለ ተቻችሎ አብሮ ለመሥራት የሚያስችል የአስተሳሰብ መደላድል አላቸው።
3. ኬንያውያን ሕገ-መንግሥታቸውን የማሻሻል ዕድልና ልምድ አግኝተዋል። ሕገ-መንግሥቱ በአገራችን እንዳለው ሆን ተብሎ እንዳይሻሻል ተስፋ-የለሽ ሆኖ የተቆለፈ አይደለም። በምርጫ የበላይነት ያገኘ ማንኛውም ድርጅት/ድርጅቶች ሥርዓቱን ተከትሎ ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ዕድል አለው። በመሆኑም የኬንያ

ሕገ-መንግሥት ቢያንስ ዘጠኝ ጊዜ ማሻሻያ ተደርጎበታል። ስለዚህ ድርጅቶች በጋራ መድረክ ተወዳድረው ወይም በፓርላማ ውስጥ የጋራ አጀንዳ ላይ በኅብረት በመንቀሳቀስ ለአገራቸው ያላቸውን ራእይ ወደ ተግባር ለመተርጎም አመች በሆነ መልክ ሕገ-መንግሥቱን ለማሻሻል ይችላሉ።

4. የአገሪቱ የመከላከያ ኃይል ተጠሪነቱና ታዛዥነቱ ለአገሪቱ ሕገ-መንግሥት እንጅ አንድ የተወሰነ ፓርቲ የሚያዘውና የሚቆጣጠረው አይደለም።
5. የቀድሞው የኬንያ መንግሥት የፖለቲካና ሰብአዊ መብቶችን በማፈን ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ብዙም የተሻለ ነበር ማለት ባይቻልም በተለይም ነፃ ጋዜጦችና ከመንግሥት ቀጥተኛ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ የመገናኛ ብዙሃን መኖር ሕጋዊ ዋስትና የነበራቸው፥ የተሻለ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚቻልበትና በዚህ ረገድ በመጠኑ ዳበር ያለ ልምድ ያለበት ሁኔታ ላይ ናቸው። በእኛ አገር እስካሁን እውን ያልሆነ በኬንያ ቢያንስ መሠረታዊ የሆኑ የቅድመ-ሁኔታ መብቶች የተሻለ ተከባሪነት አላቸው።

በነዚህ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ልዩነቶችና በሌሎችም ምክንያቶች በአገራችን በአሁኑ ደረጃችን ያለውን አገዛዝ ከሥልጣን በማውረድ በጥምር መንግሥት ለመተካት የሚደረግ እንቅስቃሴ ከምንፈልገው የሰከነ ሽግግር አኳያ የሚሠራ ሆኖ አላገኘነውም።

የጥምር መንግሥት የተሻለ የሚሠራው የመቻቻል ፖለቲካን የተለማመዱ ድርጅቶች ባሉበትና ወይም ለሁሉም እኩል የመንቀሳቀስና "የመፈታተን" ዕድል ባለበትና በሰፈነበት ሁኔታ ነው።

በአገራችን ልዩ ሁኔታ የጥምር መንግሥት አሁን ፈጽሞ አይሠራም ሳይሆን የምንለው የጥምር መንግሥት የተሻለ ዕድል የሚኖረውና ውጤታማ እንደሚሆን በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው የሰከነ መሸጋገር ካደረግን በኋላ ይሆናል ለማለት ነው። በአገራችን ያለን ድርጅቶች ያ ዕድል እስካሁን አልነበረንም። አንድ ደረጃ ይቀረናል። ያን ደረጃ መስምምነትና በጋራ እንውጣው።

ስለዚህ በኛ አመለካከት በሥልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ እንደ አንድ አካል በኅብረት ደረጃ በምርጫ ተወዳድረን ወይም ከፍ ሲል እንደጠቀስነው አገዛዙ የምርጫውን ሁኔታ ካሰናከለው ተቃዋሚው (ኅብረቱ) በሚወስደው የተቀናበረና ቀጣይነት ያለው ትግል ከመንግሥት ሥልጣን ካስወገድን በኋላ የሚኖረን የመንግሥት ዓይነት የጥምር መንግሥት ሲሆን አይታየንም።

ይኸንን ከወዲሁ ተወያይቶ መወሰን ደግሞ ለጋራ ትግላችን ጤናማና ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን የግድ ይሆናል።

ለጋራ ትግላችንና ለሁላችንም ለሆነችው አገራችን የተሻለ ሥርዓትን ለማምጣት ይበጃል ከሚል እምነት ለውይይት የምናቀርበው የመንግሥት ዓይነት ሃሳብ ላይ የሰከነ ውይይት እንደምናደርግና የሚቀርቡ አማራጮችንም ጊዜ ወስደን ለማየትና በጥሞና ለመመርመር ዕድሉ እንደሚኖር ተስፋ አለን።

**አገራችንን ከችግር አዙሪትና ከእርስ በርስ ቀውስ ለማዳንና የተደላደለ ሁኔታን ለማምጣት የምንችለው በቀጣዩ ምርጫ በጋራ የፖለቲካ ፕሮግራም ተወዳድረን የምናመጣው የመንግሥት ዓይነት ላይ የጋራ ግንዛቤና መግባባት ሊኖረን ስንችል ብቻ ነው።**

በኛ በኩል አሁን አገራችን ከምትገኝበት ሁኔታና በሁለቱም በኩል (ለመለወጥ ከተሰለፈውም ይሁን ላለመለወጥ የሙጥኝ ካለው ኃይል) አኳያ የተሻለ ሆኖ ያገኘነው የመንግሥት ዓይነት አንድና አንድ ብቻ ነው። ይኸውም የአደራ መንግሥት ነው።

ይኸን እውን ለማድረግ በቅድሚያ በተገቢ ልንመልሳቸው የሚገቡን ጥያቄዎች አሉ። እነሱም፡-

ለመሆኑ የአደራ መንግሥት ምንድን ነው? ለምንስ ያስፈልጋል? ማነው የሚመሠርተው? እንዴትስ ይመሠረታል? አሠራሩስ እንዴት ነው? የፖለቲካ ድርጅቶችስ ሚና ምን ይሆናል? ህልውናቸውስ? ወዘተርፈ......

የደርግ አገዛዝ ሲያከትም የታሪክ አጋጣሚ ሆነና ሥልጣኑን "የተረከቡት" ቡድኖች ከብስለት ጉድለትና በአብዛኛው ድርጅታዊ አፈጣጠራቸውና ድርጅታዊ አስተዳደግ ባህሪያቸው

የሚያሳድረው ተጽዕኖ የግድ ስለሚል ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች የሚሆን ብሔራዊ መግባባት ላይ የተመሠረተ የተሻለ ሥርዓት ለመመሥረት የነበረው ዕድል እንደዋዛ እንዲከስም በመደረጉ እነሆ የደረስንበት ዝብርቅርቅ ደረጃ ላይ እንድንገኝ አድርጓል።
አሁንም ወደ ቁልቁል የሚገሰግሰው የውድቀት ሂደት እንዲገታና አገሪቱ ከችግር አዙሪት እንድትወጣ የሚያስችላት፥ የመጣው ሁሉ እንዳሻው ተጫውቶባትና አድቅቋት፥ አልፎ ተርፎም አጥፍቷት ለመጥፋትም ግድ ለሌላቸው ክፍሎች ከመዳረግ ለማውጣት ዛሬ በየድርጅቱ ያለነው ምን ዓይነት የሥልጣን ወንበር እንደምናገኝ ሳይሆን ስሊቱ የሚቀጥለው ትውልድ የአሁኑና ከሱ ቀደም ያሉት ትውልዶች ያሳለፉት የመከራና የሰቆቃ ሁኔታ የማይጠናወተው ነፃና ባለ ተስፋ እንዲሆን መሆን ይኖርበታል።

በረጅሙና ጠመዝማዛ የአገራችን ታሪክ እንደምናየው ቀደም ሲል በነበሩ ባላባታዊ አስተዳደሮች እንኳ ሥልጣን ከአንድ ንጉሥ ወደ ቀጣዩ "ተመራጭ" (በአብዛው ለልጅ) ሲተላለፍ ሥልጣኑን እንዲረከብ የሚፈለገው ሰው ዕድሜው የማይመጥን ሲሆን (ሕፃን ሲሆን) ዕድሜው ሥልጣን ለመያዝና ሃላፊነቱን ለመወጣት እስከሚችል ድረስ በትውልድ፥ በችሎታና በታማኝነት ሚዛን የሚገባ ሰው በሞግዚትነት እንዲሠራ ይደረግ ነበር። ይኸ ሞግዚት ገዥ በሥልጣን ተቀናቃኞች ዘንድ (በአብዛኛው ሕዝቡ እንኳ ስሊቱ ውስጥ አይ ገባም) የሚፈራ፥ የሚከበርና የሚናገረው የሚደመጥ መሆን ነበረበት። ያ ሞግዚትም አደራውን አይበላም፤ ጊዜው ሲደርስ ሥልጣኑን ለተመዳቢው ያስረክባል።
ያኔ በነበረው በጣም ኋላ-ቀር ሥርዓት ሳይቀር በዚህ መልክ የመንግሥት ያውም ፍጹም የሆነን ሥልጣን በአደራ በመስጠት ያለ የእርስ በርስ መተላለቅ፥ መበጣበጥና የሰላም መናጋት የሥልጣን ርክክብ ይደረግ ነበር።
በዘመናችን ካምቦድያ የአደራ መንግሥት አካሄድን በመከተል ቢያንስ ሊከሰት የሚችልን ትርምስ አስወግደዋል።
ምንም እንኳ የውጭ ጠንካራ እጅ መኖሩ በተወሰነ ደረጃ በሕዝቡ ዘንድ ተአማኒነትን ሊቀንስ ቢችልም አሁን በኢራቅ የሚሞከረውም አካሄድ እንዲሁ የባሰ ትርምስና መተላለቅን ለማስወገድና የተሻለ ሽግግርን ከማድረግ አኳያ ነው።
አንዳንድ ወገኖች "ለአንድ አገር የአደራ መንግሥት የሚያስፈልገው ያ አገር መንግሥት ሳይኖረው ሲቀርና ማእከላዊ የሥልጣን ክፍተት ሲኖር ብቻ ነው ፤ በኛ አገር ጠቀመም አልጠቀመ፥ ወደድነውም አልወደድነው መንግሥት አለ ስለዚህ ይኸ አስተሳሰብ አይሠራም፥ ወዘተ...." ሲሉ ተደምጠዋል።
በአንድ በኩል ልክ ናቸው። ወደድነውም ጠላነው፥ ተቀበልነውም አልተቀበልነው መንግሥት አለ። ጥያቄው ግን ያለውን መንግሥት ከመውደድና ካለመውደድ ላይ አይደለም። ዋናው ጥያቄ ይኸ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት አሠራር፥ አካሄድና አመራር አገሪቱን ወዴት እየወሰዳት ነው? ነው። ጥያቄው አሁን አገራችን በምትሄድበት መንገድ የተጓዙ አገሮች የደረሰባቸው ሰቆቃ በኛ ላይ እንዲደገም እንፈልጋለን ወይ? ነው።
ለሁላችንም (በሥልጣን ላይ ላለው አካል ጭምር) የሚበጅ፥ ከአሁን በፊት በሚያሳዝን መልክ አመለጠን የምንለውና የምንቆጭበት፥ የሰከነ ሰላማዊ ሽግግር ማድረግ አለብን? እንችላለን? ወይስ አቅሙም፥ ችሎታውም በተለይ በጎ ፈቃዱ የለንም? ነው የምንለው።
ያለው መንግሥትማ ወደ ጋራ ጥፋት እየወሰደን ነው። ለአገሪቱ የሰከነ ሽግግር ሊያመጣ አልቻለም፥ አይችልምም።
በሥልጣን ላይ ካለው መንግሥት፥ በተለይ አገራቸውን አጥፍቶ ለመጥፋት የማይፈልጉና ሃላፊነት ከሚሰማቸው ወገኖች በኩል የሚጠበቀውና ግፊቱንም ማጎልበት ያለብን ለዚህ የጋራ ጥረት ፈቃደኛና ተባባሪ በመሆን አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ነው።
ገልብጠው ካዩት ይኸንንን ያለማድረግ አማራጩ ለአገሪቱም ሆነ በተለይ ለነሱ ለራሳቸው ፈጽሞ አይበጅም።

የአደራ መንግሥት ማለት በአንድ አገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ከመሻሻል ወደ መባባስ የመሄድ አጋጣሚው ጎላ ብሎ ሲታይና በአንጻሩ ሊከሰት የሚችለውን የሥልጣን ሽኩቻ፥ አለመረጋጋት፥ የርስ በርስ ቀውስ፥ ብጥብጥና መፋጀት ሊያረግብ የሚችል በግልጽ

የወጣ አማራጭ የሚሆን ኅላ ያለና የሚታይ፥ በሕዝብም ዘንድ ተደማጭነትን፥ ከበሬታንና አመኔታን የሚያገኝ ኃይል በማይኖርበትና ማዕከላዊ የሥልጣን ክፍተት የመፈጠር ዕድል በሚኖርበት ጊዜ ለሁሉም የሚሆን የተረጋጋ ሁኔታን ለማስፈን በስምምነት የሚቋቋም ጊዚአዊ አስተዳደር ነው።
የአደራ መንግሥት አስፈላጊነት በተለይ እንደ አገራችን ኢትዮጵያ ባሉ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ለመዘፈቅ የተመቻቸ አደገኛ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ አገሮች መረጋጋትን ማስገኛ፥ ተፈላጊና ጤናማ የመሸጋገሪያ መንገድ ነው።
የተዘበራረቀ የፖለቲካ ሁኔታ፥ ያልዳበረ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት በሌለበትና በተጨባጭ ግልጽና በማያሻማ መልክ ብሔራዊ አመኔታን፥ ተሰሚነትንና ከበሬታን ሊያስገኝ የሚችል አንድ ወጥ አካል በሌለበት አገር፥ ብጥብጥና የሰላም መናጋትን ለማስወገድ የሚመረጠው የሰከነ ሽግግር ማምጣት የሚችልና ከፖለቲካ ሥልጣን ተፎካካሪዎች ውጭ በሆኑ ወገኖችና ክፍሎች የሚመራ አካል እንዲኖር ዕድል ሲሰጠው ብቻ ነው።
ብሔራዊ ኃላፊነት የማይሰማው፥ ደንታ ቢስና ልዩነት ማስፋትን እንደ ፖሊሲና የአገዛዝ መሣሪያውና መመሪያው ያደረገ መንግሥት ባለበትና በተቃዋሚው ክፍል ሳይቀር የመቻቻልና የመከባበር የፖለቲካ ባህል በሌለባት አገራችን የሰከነ ሽግግርን ማድረግ የምንችለው የሁላችንንም፥ ቢያንስ የአብዛኛውን ሕዝብ፥ አመኔታና ሙሉ ትብብር ያገኘ የአደራ መንግሥት ሲኖረን ብቻ ነው። የሚያስፈልገንም ለጋራ ጥቅማችን፥ አገራዊና ብሔራዊ ደኅንነታችና የወል ኅልውናችንን ለማስጠበቅ ነው።
ይህ በአንድ በኩል ገለልተኛ በሌላ በኩል በሁሉም ዘንድ ተቀባይነትና አመኔታ ያለው አካል በአደራ መንግሥትነት ለተወሰነ፥ ከአንድ ዓመት እስከ አንድ ዓመት ተኩል፥ ለሚሆን ጊዜ አገሪቱን በበላይነትና በማዕከላዊነት ያስተዳድራል።

በልዩ ልዩ መንገድና መልክ ለእኩልነትና አንድነት፥ ለሕግ የበላይነትና የሰብአዊ መብት መከበር ያለመታከት፥ በጣም ለረዥም ጊዜ አንዳንዶች ዕድሜ-ልክ፥ የታገሉ ሁሉ በአሁኑ የቀውጢ ወቅት ልዩ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባው ጉዳይ የአገራቸውን ሰላምና አንድነት አስገኝተው የነደፉትንና የሚታገሉለትን ፕሮግራም ያለምንም ስጋትና ማዕቀብ ለሕዝባቸው ማቅረብና ማስተማር የሚችሉበትን የተሻለ ሁኔታ ሊያመጣ ለሚችል ሂደት መሆን ይኖርበታል።
ሰላምንና መረጋጋትን አስገኝቶ ወደ ተሻለ የብዙኃን ሥርዓት የረጋና የሰከነ ሽግግር ማድረግ የሚቻለው በዚህ መንገድ ስንጓዝ ብቻ ነው።

ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ፕሮግራም ነድፎና መዋቅሩን ዘርግቶ የሚታገለው ለፖለቲካ ሥልጣን ለመብቃት ነው። ይህ መሠረታዊ፥ ግልጽ የሆነና የማያጠያይቅ ነገር ነው።
የፖለቲካ ድርጅቶች ለተወሰነ ጊዜ በፍላጎታቸው በራሳቸው ላይ የሥልጣን ማዕቀብ መጣል ሊኖርባቸው ነው። እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ድርጅቶቹና መሪዎቻቸው መስዋዕት እንዲያደርጉ የሚጠየቁት የሥልጣን ጥያቄ ጊዚያዊ መሆኑንና እንዲያዉም ለተሻለ ዕድልና ሁሉም አትራፊ የሚሆንበትን ሁኔታ ለማስገኘት መሆኑን ነው።

አንዳንድ ድርጅቶች የአደራ መንግሥት መኖር አንድም የታገሉበትንና ለድል ባለቤት የሆኑበትን አሳልፎ እንደመስጠት በሌላም በኩል ኅልውናቸውን በእጅጉ የሚፈታተን እንዲያውም የሚያጠፋቸው አድርገው ሊወስዱት ይችላሉ።
መቸም የዚህ ዓይነት ሥጋትና ድምዳሜ ላይ የሚደርስ ድርጅት በያዘውና በቆመለት የዓላማ ጥንካሬ የማይተማመን ወይም አርቆ ማየት ችግር ያለበትና የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ሕዝብ ብቻ መሆኑን የማያምንና የማይቀበል ወይም የዘነጋ፥ አለያም የአገሪቱን የችግር መጠንና ጥልቀት ከልብ ያልተገነዘበ ብቻ ነው።
በኛ እምነት እንደዚህ ዓይነት ድርጅት አላጋጠመንም፥ ይኖራል የሚል ግምትም የለን። ካለም እንደሌለ መቁጠሩ ይሻላል።
በሃቅና በግልጽ እንነጋገርና አሁን ባለንበት ሁኔታና ጊዜ ለመሆኑ የትኛው ድርጅት ነው በሕዝብ ዘንድ ሰፊና ሙሉ አመኔታን የሚያገኝ? የትግል ልምዱም ሆነ አደረጃጀታቸው

ለፖለቲካ ሥልጣን የሚያበቃቸው ድርጅቶች ባይጠፉም ቁልፉ ጥያቄ በጠቅላላው ሕዝብ ይቅርና በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል እንኳ ሙሉ በሙሉ አመኔታን ማግኘት ቀርቶ አመኔታን ለማምጣት የሚችል ማነው? ነው::

ይኽ ግን የድርጅቶቹ ብቻ ጥፋት ወይም ጉድለት ሆኖ መታየት የለበትም:: ድርጅቶቹ የሕዝብን አመኔታና ከበሬታን ለማግኘት እነሱነታቸውንና ማንነታቸውን ለማስመስከርና ለማረጋገጥ ዕድሉ ኖሮአቸው አያውቅም፥ አልተፈጠረላቸውምም::

ይኽ ደግሞ በኛ አገር ብቻ የተከሰተ ወይም ኢትዮጵያዊ ስለሆንን የወረደብን መዓት አይደለም:: ያለፉት ሰላሳ ዓመታት የፖለቲካ ውጣ ውረድ ያተረፈልን የደፈረሰ ሁኔታ ውጤት ነው:: ድርጅቶቹ ደግሞ የአገሪቱ ሁኔታ ውልዶች ናቸው:: በመሆኑም ከፈጠራቸው ሁኔታ ውጭ ሊሆኑ ያዳግታቸዋል::

በካምቦዲያ፥ በሶማሊያ፥ በላይቤሪያ፥ በሴራሊዮን፥ ወዘተ... የታየው ዘግናኝ ክስተት የሰከነ ሽግግር ማድረግ ካለመቻል የመነጨ እንጅ እነሱ ስለሆኑ ወይም ሰብአዊ ተፈጥሮ ስለጎደላቸው የተፈጸመ ተግባር አይደለም::

በማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል የሚነሱ ብሶት የወለዳቸው ጥያቄዎችን በቀና መንፈስ፥ በትክክልና አግባብ ባለው መንገድ በቶሎ አይቶና ተረድቶ በውይይት ለመፍታት በቂ ጥረት አለማድረግ ችግርን አይፈታም:: ብሶትን ሳይረዱና ለጥያቄው በወቅቱና በተገቢ ምላሽ ሳይሰጡ ጥያቄ ያቀረበውን ክፍል መወንጀልም ሆነ መኮነን ወይም በጉልበት ለማንበርከክ መሞከር የለየለት እብደት ነው:: ይኽን ማድረግ ጉዳዩ እየከረረ የሰው ልጅ አውሬአዊ ተፈጥሮ ጎኑ ብቅ እንዲልና እንዲያብብ ዕድል መስጠት ይሆናል:: ውጤቱም በልዩ ልዩ የዓለማችን ክፍሎች ባሉ አገሮች ውስጥ አብሮ በኖረና የጋራ ታሪክ ባለው ሕዝብ መካከል ያየነውን ማመን የሚያዳግት ዘግናኝ የርስ በርስ መተላለቅ ነው:: በዚህ ሰቆቃ ተጎጅው ሁሉም ነው::

በአንጻሩ አንዳንድ ጥያቄውን በግንባር ቀደምነት ያነገቡ ክፍሎች ከብሶቱ ተገቢ መነሾ በመራቅ፥ ጥያቄውን በተዛነፈ መልክ በማቅረብና ያለቅጥ በመለጠጥ እራሳቸውን እንደ ብቸኛ ተጠሪና ወኪል ከመቁጠር ጀምሮ የብሶቱን መንስዔ ሊያድበሰብስና ጨርሶም ዋጋ ሊያሳጣ የሚችል ተግባራት ውስጥ በመግባት ሁኔታውን የባሰ የሚያወሳስቡበት ሁኔታ አለ:: የዚህ ዓይነት ሁኔታ ደግሞ ለአፈ ጮሌዎችና ለጥላቻ አበጋዞች በጣም አመች ነው:: በእንደዚህ ያለ የቀውጢና የውዥንብር ወቅት የአስተዋይና የአርቆ ተመልች ወገኖች ድምጽ ይሰልላል፥ ይዘጋል:: አንዱ የሌላውን ችግር ለመረዳት ሁኔታው ይጠባል፤ ጊዜ የለም፤ አንዱ ሌላውን መኮነንና ተጠያቂ ማድረግ ይበዛል፤ መደማመጥ አይኖርም:: ሁሉም እራስን በመከላከል ስም "በየጓዳው" ይከትማል:: የሰው ልጅ አውሬአዊ ባህሪ ማመን በሚያዳግት መልኩ ጎልቶና አብቦ ይወጣል:: እርስ በርስ መተላለቅ ዋና ሥራ ይሆናል:: የእብድ መንደር ይሆናል::

በቀድሞ ዩጎዝላቪያ፥ በሶማሊያ፥ በላይቤሪያ፥ በኮንጎ፥ በምሥራቅ ቲሞር ወዘተ... የተከሰተው ሁሉ በጥሞናና በቀጥታ ብሶትን ማስተናገድና ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በውይይት መፍታት ካለመቻል የመጣ እንጅ በግድ ችግሩ መድረስ ስላለበት ወይም እንዳይደርስ ማድረግ ስለማይቻል ወይም የነኝህ አገር ሕዝቦች የተፈጥሮ ባህሪ የተለየ ስለሆነ አይደለም:: በአንዳቸውም ቢሆን የተከሰተው አደጋ ከመፈጸም መወገድ ስለማይችል አልነበረም ጉዳቱ የደረሰው:: የዚህ ዓይነት አደጋ መወገድ የሚችለው ግን ችግሩ ከመፈንዳቱ በፊት አስቀድሞ ሁኔታውን የሚያረግቡ ቀጥተኛና ቅን እርምጃዎች መውሰድ ሲቻል ብቻ ነው:: ይኽም የሚመጣውና እውን የሚሆነው ለብሔራዊ መግባባት አመች ሁኔታ መፍጠር ሲቻል ነው::

በአንፃሩ በደቡብ አፍሪቃ የታየው በክቡር አቶ ኔልሰን ማንዴላ የተመራው የአፍሪቃ ብሔራዊ ኮንግረስ ፍጹም የሆነ አርቆ አስተዋይ፥ ከራስ ወዳድነትና ከሥልጣን ጥም የተላቀቀ፥ በአገርና በወገን እውነተኛ ፍቅር የታነፀ፥ ካለፈው በደል የበለጠ የወደፊት የጋራ ዕድልን ቅድሚያ የሰጠ ብሔራዊ መግባባትን ያስገኘ አመራርና እንቅስቃሴ ለማንም የርስ በርስ መጠፋፋትና መተላለቅን ለማይፈልግ፥ የጋራ ብልጽግናን፥ እድገትንና ብሩህ ተስፋን የሚያመጣ ሥርዓትን የሚሻ ሕዝብ በጥሩ ምሳሌነትና በአርአያነት ሊከተለው የሚገባ ድንቅና በጎ ምግባር ነው::

ለደቡብ አፍሪቃውያን ወገኖቻችን በዘግናኙ የአፓርታይድ ሥርዓትና በአራማጆቹ ከደረሰባቸው ይኽ ነው የማይባል ሁለ-ገብ በደል የበለጠ ያተኮሩበትና ሚዛን የደፋው የወደፊቱ የጋራ ዕድላቸው በመሆኑ ያለፈው ጥፋት እንዳይደገም የሚቀሰመውን ትምሕርት ቀስመው፥ ጥፋቱንና በደሉን ላይመለሱበት በጋራ ቀብረው ከኮሚኒስቱ እስከ ቀኝ አክራሪው ሳይዘባሩ በኅብረት የተረባረቡት ለሁሉም የምትሆን የወደፊቷ አገራቸውን በማቆየት ላይና የሁሉንም ዜጎች መብት የሚያስከብርና ወደ ብልጽግናና ልማት የሚወስዳቸው የተሻለ ሥርዓት ግንባታ ላይ ነው::

ያንን ማድረግ በመቻላቸውና በመታደላቸው ይኸውና ደቡብ አፍሪቃን እንደ አገር ማቆየት ብቻ አይደለም ከኢትዮጵያ ሳይቀር ለልዩ ልዩ አገር ዜጎች መሰደጃና መጠለያ ለመሆን አብቅተዋታል::

እዚህ ላይ በመጥፎና በመልካም ምሳሌነት የጠቀስናቸውን ክፍሎች ያነሳነው አገራችን መንትያ መንገድ ላይ መሆኗን ለማስገንዘብና የሁኔታውን የምር አሳሳቢነት ከልብ በማጤን የተሻለውን መንገድ እንድንይዝ ለማሳሰብ ነው::

የመማማርና የመቻቻል ፖለቲካን መከተል በጣም ትልቅነትና የብስለት ምልክት ነው::

በአገራችን ማንዴላዊ ተክለሰውነትና አስተሳሰብ ያለው ባይኖርም አገሩንና ወገኑን ለመታደግ በጋራ ማንዴላዊ ተግባር ላይ ለመሰማራት ቁርጠኝነቱ ያላቸው ብዙዎች እንዳሉ አንጠራጠርም:: ይቻላል!!

ለመሆኑ አደራ ባዩ ማነው? የማነው አደራ? አደራ ተቀባዩስ?

አደራ ሰጭው ክፍል በልዩ ልዩ መልክ የተደራጀው ወገን ነው:: ባለ አደራው ደግሞ ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: እዚህ ላይ አደራ ሰጭው የተደራጀው ክፍል ከሆነ፥ አደራው ታዲያ ለኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ ሳይሆን ለድርጅቶቹ አይሆንም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: አዎን:: ግን የድርጅቶቹ ትግል ሕዝብን ለሥልጣን ለማብቃት ስለሆነና ሥልጣንንም ማግኘት ያለባቸው የሥልጣን ምንጭና አንጡራ ባለቤት ከሆነው ከሕዝቡ ብቻ በመሆኑ በዚህ ለሁሉም የሚሆን ሥርዓትን ለማምጣት በሚደረግ ትግል የሕዝቡ አደራ የድርጅቶችም ጭምር አደራ ስለሆነ ነው::

የአደራ መንግሥት እንዴት ይቋቋማል?

የአደራ መንግሥት እንደየ አገሩ ልዩ ሁኔታ በልዩ ልዩ መልክ ሊቋቋም ይችላል::

ሆኖም መሠረታዊ የሆኑ ከሞላ ጎደል ለሁሉም የሚሠሩ እውነታዎች አሉ:: ከነዚህ ዋናው ከአመሠራረቱ ሂደት ጀምሮ በሕዝብ ዘንድ <u>ተአማኒነትና ተደማጭነት</u> ያለው የመሆን ብቃት ነው::

በአጥጋቢ ሁኔታና በቀነሰ ችግር መሥራት ይቻለው ዘንድ <u>የአደራ መንግሥት በሕዝቡ ፍላጎትና በፖለቲካ ድርጅቶች ይሁንታና ትብብር ይቋቋማል</u>::

የአደራ መንግሥት ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከፖለቲካ ሥልጣን ፉክክር፥ ውድድርና ፍላጎት ውጭ ከሆኑ የሙያ ማኅበራት፥ ከማኅበረ-ሰብ ስብስቦች፥ ከምሁራን፥ በተቻለ መጠን የአገሪቱን የብሔረሰብ ስብጥር በወከለ መልኩ ታዋቂ ግለሰቦችን ያካተተ ሆኖ ከተውጣጣ አካል ሊቋቋም ይችላል::

እንደ አገራችን ባሉ የተወሳሰበ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙና በአንጻሩ በሁሉም፥ ቢያንስ በአብዛኛው ወገን ተቀባይነት ያለው፥ ከበሬታንና ተደማጭነትን ያተረፈ ነጥሮ የወጣ መሪ የፖለቲካ ድርጅት በሌለበት አገር የሚቋቋመው የአደራ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶችን ባላቀፈ (ባልጨመረ) መልኩ መሆኑ ይመረጣል::

የፖለቲካ ድርጅቶችና ከላይ የተጠቀሱት በፖለቲካ መልክ ያልተደራጁ ክፍሎች በጋራ የሚያቋቁሙት መንግሥት አብዛኛውን ጊዜ ከአደራ መንግሥትነት ይልቅ የሽግግር መንግሥትነት ባህሪ ይኖራቸዋል::

አሁን አገራችን ባለችበት ልዩና ውጥንቅጥ ሁኔታ ግን በኛ በኩል የአደራው መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶችን ባይጨምር በጣሙን የተሻለ ነው::

በዚህ የአደራ መንግሥት ውስጥ በኃላፊነት የሚመደቡና የሚሳተፉ ወገኖች የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፤

1. በእኩልነት የሚያምን/የምታምን፥
2. ሚዛናዊ አመለካከት ያለው/ያላት፥
3. ከጎጠኛና ጎሠኛ አመለካከት የፀዳ/የፀዳች፥
4. በሕዝብና በአገር ላይ በደል ያልፈፀመ/ያልፈፀመች፥
5. በሕዝብ ዘንድ አመኔታን፥ ተደማጭነትን፥ከበሬታንና ተቀባይነትን ያገኘ/ያገኘች ወይም ማግኘት የሚችል/የምትችል፥
6. የሥልጣን ጥመኛ ያልሆነ/ያልሆነች፥

<u>የአደራ መንግሥቱ ተግባራት</u> ፤

የአደራው መንግሥት ከሚኖሩት በርካታ ተግባሮች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ሆነው እናገኛቸዋለን።

1. በማእከላዊ ሃላፊነት የአገርን አንድነትና ፀጥታ ማስከበር፥
2. በየትም ቦታ የሚገኙ የሁሉንም ዜጎች መሠረታዊ የፖለቲካና ሰብአዊ መብቶች ማስጠበቅ፥
3. ለመሻሻል እንኳ ዕድል እንዳይኖረው ተጠላልፎና ውትፍትፍ ተደርጎ በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገውን የሕዝብን ይሁንታ ያላገኘ "ሕገ-መንግሥት" በአዋጅ ማንሳት፥
4. የአደራው መንግሥት የሚሠራበትን መመሪያ (ቻርተር) በግልጽ ማውጣትና ማሳወቅ፥ (ሰነዱ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን የተቀበለና የሚያከብር ይሆናል)፥
5. በልዩ ልዩ ምክንያት በመሣሪያ ትግል ላይ ለተሰማሩ የሰላም ጥሪ ማቅረብና በሰላማዊ መንገድ ለጋራ ሰላማዊ ሽግግር እንዲሰሩ አስፈላጊውን ትብብርና እርዳታ ማድረግ፥
6. በስደት የሚገኙ ዜጎች በሰላም ተመልሰው በአገራቸው ግንባታ ላይ እንዲውሉ ጥሪ ማቅረብና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፥ አስፈላጊውን እርዳታና ትብብር ማድረግ፥
7. የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ነፃነትና ያለምንም ስጋት የፖለቲካ ድርጅታቸውን የማስተዋወቅም ይሁን ሕዝብን የማስተማርና የማደራጀት መብታቸውን በሕግ ማወቅና ሙሉ ዋስትና መስጠት፥
8. ለጋራ ሰላም፥ እድገትና ብልጽግና ሲባል ቀደም ሲል በነበሩም ይሁን አሁን ባሉ ማናቸውም ሥርዓት፥ ድርጅት፥ ወዘተ... ውስጥ ተሳታፊ የነበሩና የሆኑ፥ በግልና ለግል ጥቅም ሲሉ ብቻ ወንጀል ያልሠሩ ወገኖች ሁሉ አባል በመሆናቸው ብቻ እንደማይወነጀሉ፤ በሕዝብና ወገን ላይ ወንጀል በመፈጸም የሚጠረጠርም ቢሆን ሙሉ መብቱ ተጠብቆ በሕግ ፊት ወንጀሉ እስከሚረጋገጥ ድረስ እንደወንጀለኛ እንደማይቆጠር በማረጋገጥ፥ በሥልጣን ላይ በነበሩ ጊዜ የነበሩበትና ያሉበት ሥርዓት ባሰፈነው ተጽእኖና ሁኔት አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ባደረሱት ወይም አድርሰናል ብለው በሚያስቡት ጥፋታቸው ለሚደነብሩ፥ በዚሁም ምክንያት በመስጋት ከአገር ሰላም ይልቅ በግላቸው ላይ ሊደርስ ይችላል ብለው ከሚያስቡት ጭንቀት የተነሳ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አፍራሽ ተግባር ላይ የመዋል አዝማሚያ ላይ እንዳይሠማሩና አገሪቱ ያስተማረቻቸውን ሙያና እውቀት፥ ያላቸውንም ችሎታ ሁሉ በአገር መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ላይ እንዲያውሉ የ"ይቅር ተብለሃል" ጥሪ እና <u>የጅምላ ምኅረት ማድረግ፥</u>
9. ለሰከነ የፖለቲካ ሽግግር የሚያበቁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፥ አገራችንንን ወደ ብልጽግናና ዘመናዊ እድገት የሚወስድ፥ እኩልነትና አንድነትን የሚያስከብር ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት የሚያስችል ሁኔታን ማደላደል፥

10. አገሪቱ በሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሕዝቡን አሜኔታ ያገኘ ሕገ-መንግሥት ባለቤት እንድትሆን የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ሸንጎ እንዲሰየም ማድረግ፥
11. ከግል ቂም በቀል፥ ከአምባገሮ፥ ከብጥብጥና ቅጥ ካጣ የርስ በርስ መጠራጠር ለመላቀቅና በሙሉ ልብ ወደ ተሻለ ሥርዓት ግንባታ ለመጓዝ ይቻል ዘንድ አገራዊ እርቅና ሰላም እንዲኖር ለማስቻል ለዚሁ ጉዳይ ልዩና ገለልተኛ አካል (ኮሚሽን) ማቋቋምና አስፈላጊውን ሁሉ እርዳታ ማድረግ፥

የአደራ መንግሥቱ እነኝህን ሃላፊነቶች ለመወጣት፣
1. የአገሪቱን የመከላከያ፥ የፖሊስና የፀጥታ ኃይሎች በቀጥታ ይቆጣጠራል፥
2. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፥

<u>የአደራ መንግሥቱ አሰያየምና አመራረጥ፣</u>
የአገራችንን ልዩ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የአደራው መንግሥት ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት በአንዱ ዓይነትና አካሄድ ሊመረጥ ይችላል።

1. <u>በጠቅላላ አገራዊ ጉባዔ፣</u>
   ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል (ማኅበራትን፥ ስብስቦችን፥ ምሁራንና ታዋቂ ግለ-ሰቦችን) እና የፖለቲካ ድርጅቶች (የኢሕአዴግ ጭምር) ተወካዮችን ያካተተ ጉባዔ በመጥራት ሁሉም በተቀበላቸውና ባፀደቃቸው መመሪያዎች መሠረት የአደራ መንግሥቱን ዋና ዋና ሃላፊዎች ማለትም ፕሬዘደንትና ጠቅላይ ሚኒስትር በምርጫ ይሰይማል።
   ጠቅላይ ሚንስትሩ የመንግሥት ዘርፍ ኃላፊዎችን (ሚኒስትሮችን) ይሰይማል።
2. <u>በቀጥታ ኅብረቱ መራጭ በመሆን፣</u>
   እያንዳንዱ የኅብረቱ አባል ድርጅት በበጎ ፈቃድ፥ በአገራዊና ወገናዊ ታሪካዊ ኃላፊነት መንፈስ ለአደራው መንግሥት ከፍ ብሎ በተጠቀሱት ወይም ሌላ በጋራ ስምምነት በፀደቁ መመዘኛዎች መሠረት ብቃት ያላቸውንና አሜኔታ የሚያሳድርባቸውን ግለሰቦች ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍል አንድ አንድ ሰው በቀጥታ በመምረጥና በጋራ በማጽደቅ ሊሰይም ይችላል። ወይም ፕሬዘደንቱን፥ ጠቅላይ ሚንስትሩን፥ የውጭ ጉዳዩንና የአገር መካላከያ ኃላፊዎችን (ሚኒስትሮችን) በስምምነት መርጦ ይሰይማል። የአደራው መንግሥት አባላት አመራረጥና አሰያየም በተቻለ መጠን በመግባባትና በስምምነት መሆን ይኖርበታል። በአንድ የአደራ መንግሥት እጩ አባል ላይ በብቃትም ይሁን በእምነት ወይም በሌላ ጉድለት ምክንያት የጠበቀና የከረረ ተቃውሞ ሲገጥምና በመግባባት ፈጽሞ መፍታት ካልተቻለ፥ እጩውን ያቀረበው ክፍል ሌላ አማራጭ እንዲያቀርብ ዕድል ሊሰጠው ይችላል። ሆኖም እጩ አባሉ በታጨበት ቦታ እንዲኖር ተመሳሳይ ጠንካራ ግፊት ሲያጋጥም በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ይወሰናል።
3. <u>ገለልተኛ መራጭ አካል በመወከል/በመሰየም፣</u>
   3.1 ከኅብረቱ ሁለት ሦስተኛ ከሙያና ሲቪክ ማኅበራት አንድ ሦስተኛ ተመራጮችን ያቀፈ ገለልተኛ የአደራ መንግሥት መራጭ አካል በማቋቋም ይኸ አካል የመረጣቸው ኃላፊዎች ላይ የመስማማት መብት መራጭ አካሉን ላቋቋሙት ክፍሎች በመስጠት ወይም ይኸ ገለልተኛ አካል የመረጣቸውን ያለ ተቃውሞ ለመቀበል ከመጀመሪያው ለሁሉም ግልጽ ሆኖ የአደራ መንግሥቱን ማቋቋም፣
   3.2 ከፖለቲካ ድርጅቶች ውጭ የሆነ ሆኖም ግን የፖለቲካ ድርጅቶቹ (ኅብረቱና ኢሕአዴግ ጭምር) የተስማሙበት ገለልተኛ አካል በማቋቋም የአደራ መንግሥቱን መሰየም ይቻላል። የአደራ መንግሥቱ በዚህ አካሄድ እንዲሰየም ከሆነ የፖለቲካ ድርጅቶቹ በአደራ

መንግሥቱ ዋና ዋና ኃላፊዎች (ፕሬዘደንት፥ ጠቅላይ ሚኒስቴር፥ የአገር መከላከያ፥ የውጭ ጉዳይና የአገር ውስጥ ጉዳይ) ሚኒስትሮች መረጣ ላይ ድምጽ ሊኖራቸው ይገባል።

በሚቋቋመው አደራ መንግሥት ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት ዋና ዋና የሃላፊነት ዘርፎች፥ ማለት ፕሬዘደንት፥ ጠቅላይ ሚኒስትር፥ የአገር መከላከያና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ውጭ ላሉ የሃላፊነት ቦታዎች ችሎታና ልምድ ያላቸው የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችም ይሁኑ የድርጅት አባላት ለሚመጥኑትና የተሻለ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ ይችላሉ ለሚባሉበት የሃላፊነት ቦታ በስምምነት ሊመደቡ ይችላሉ። ይኸ ሲሆን ግን ለሃላፊነት የታጨው/የታጨችው ግለሰብ በሃላፊነት ላይ ሲመደብ/ስትመደብ አባል የሆነበትን/የሆነችበትን ድርጅት በመወከል ሳይሆን ለመመረጥ ባበቃው/ባበቃት ሙያ ብቻ ይሆናል። ይኸ ሁኔት ሲያጋጥም ግለሰቡ/ግለሰቧ የተመደበበት/የተመደበችበት የሃላፊነት ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ከድርጅት አባልነት ይርቃል/ትርቃለች ፥ የድርጅት አባል አይሆንም/አትሆንም።

የአደራው መንግሥት የሚተካው በነፃና ርቱዓዊ ምርጫ ተወዳድሮ ባቸነፈ ድርጅት ወይም ድርጅቶች በሚቋቋም ሕገ-መንግሥታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ብቻ መሆን አለበት።

ለመሆኑ በዚህ የአደራ መንግሥት ጊዜ የፖለቲካ ድርጅቶች ምን ይሠራሉ?
የፖለቲካ ድርጅቶች ፥ የኅብረቱ አባላትም ይሁኑ አሁን አባል ያልሆኑ (በሥልጣን ላይ ያለው ድርጅትም ጭምር)፥ በሽግግር መንግሥቱ ጊዜአዊ አስተዳደር ወቅት ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ተግባራት ይኖሯቸዋል ማለት ይቻላል።
1. የአደራው መንግሥት የሚመራበትን አገር የማስተዳደሪያ ጊዜአዊ መመሪያ (ቻርተር) ከተሰያሚዎቹ ጋር በመሆን በጋራ ይቀርጻሉ/ያወጣሉ፥
2.ይህ የአደራ መንግሥት በሚሰጠው ዋስትና በመጠቀም የፖለቲካ ድርጅቶች እስካሁን በአገራችን ያልታየውና ሁሉም የታገሉለትንና የሚታገሉለትን መብት እውን በማድረግ ያለ ምንም ፍራቻና ስጋት፥ በሙሉ ነፃነት የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን በማስተማርና ሕዝቡን በማደራጀት፥ የድርጅቶቻቸውን ድርጅታዊ አቅም ያዳብራሉ፥ በአገሪቱ የፖለቲካ ሕይዎት ውስጥ የተሻለ ተደማጭነት እንዲኖራቸውና ምናልባትም በአገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያው ለሚሆነው እውነተኛ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ እራሳቸውን ያዘጋጃሉ።
3. የአደራው መንግሥት በአደራ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ እንዳይሄድ ይከታተላሉ።
4. የአደራው መንግሥት ሃላፊነቱን በሚገባና ያለ ብዙ ችግር እንዲወጣ አስፈላጊውን ትብብር በማድረግና የሚጠበቅባቸውን ብሔራዊ ኃላፊነት በመወጣት ለጋራው ጥረት መሳካት የግላቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

## ፬ ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች (ኢዴኃኅ) በተመሠረተበት መንፈስ ለአገራችን ውስብስብና እየከፋ ያለ ሁኔታ አሁንም የጋራ ምላሽ ከማስገኘት ውጭ ለሁላችንም የሚሆን የተሻለ አማራጭ መንገድ የለንም።

*እንደ እውነቱ ከሆነ በጋራ ቆመን ችግራችንን ጨርሶ ለማስወገድ ቀርቶ አብዛኛውን እንኳ ለመቅረፍ የሚደረገው ትግል አቀበት ነው:: ይኸም እንዲሆን ያደረግነው እራሳችን የፖለቲካ ድርጅቶች መሆናችንን ማመንና መቀበል ይኖርብናል::*

*በአሁኑ ጊዜ በጋራ በመሥራት ያለ የሌለ ኃይላችንን የምናስተባብርበት እንጅ ተነጣጥለን የምንጓዝበት ሁኔታ ላይ አይደለም ያለነው:: ተለያይቶ ለመታገል መከጀል በውነት ከቅንጦት ይቆጠራል:: ለቅንጦት ደግሞ ቢያንስ ጊዜው አይደለም:: አገር በሚከፈል የሕይዎት መሥዋእትነት ብትበለጽግ ኖሮ አገራችን የትና የት በደረሰች:: ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ የትግል ዘርፍ ረግፈዋል:: ይኽ እልቂትና መበላላት አንድ ቦታ ላይ መቆም አለበት:: የማክተሚያውን ጊዜ አሁን እናድርገው:: ይኽ ደግሞ ስለተመኘነው ወይም ስላወራነው ወይም ተሃስቦአችንን በአጽንዖትና በምሬት ስለገለጽን እውን አይሆንም:: መሠረታዊ የሆነ የአስተሳሰብና የእምነት ለውጥ በራሳችን ላይ ማድረግ ስንችል ብቻ ነው ሁኔታውን መቀየር የምንችለው:: በቅድሚያ እራሳችንን ሳንቀይር ደግሞ ሁኔታን መቀየር ፈጽሞ የማይሆን ነገር ነው:: ድርጅቶችን ያገናኘ የአገርና የወገን እንጅ የግል ጉዳይ አለመሆኑ ምን ጊዜም መዘንጋት የለበትም:: ስለሆነም በተቻለ መጠን አጉል ጥርጣሬና ያለመተማመን አባዜን አስወግደን ትኩረታችን ያገናኘን ዓላማ ላይ መሆን ይኖርበታል::*

*እንደ ማንኛውም አምባ ገነንና ያለ ሕዝብ ፍላጎትና ይሁንታ ወደ ሥልጣን የመጣና ሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት በአገራችን ላይ ያለውም የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በሥልጣን መቆየትን ብቻ የኀልውናውና የሕይወቱ ዋና ዋስትና አድርጎ መውሰዱ የታወቀ ነው:: ስለዚህም ነው የሚደርስባቸውን የተቃውሞ ሃሳብ ሁሉ ለአገርና ለወገን ከመጥቀምና አለመጥቀም አኳያ ሳይሆን ራሳቸውን በግለሰብ ደረጃ የመኖር ዋስትናቸውን የሚነሳቸው አድርገው የሚያዩት:: ይኸን ስጋት በሥልጣኑ ዙሪያ ያሉ ተባባሪዎቻቸውም የሚጋሩት ነው:: እነሱ ሊገነዘቡት የሚገባው ግን ሥጋታቸው እውን የሚሆነው ከያዙት የሕዝብ ብሶት የወለደው ቁጣን ከሚጋብዝ ፖሊሲና አሠራር እራሳቸውን በሰላም ሲያስወግዱ ብቻ መሆኑን ነው::*

*በአንጻሩም የነግይቱ የተሻለችና የሁሉም ዜጎቿ መብት የሚከበርባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚታገሉት ኃይሎች በማያሻማ መንገድ ግልጽ ማድረግ ያለባቸው አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ክፍል በተጓዘበትና እሱ በተካው የደርግ ሥርዓት ውስጥ የተሳተፈውን ወገን ሁሉ እንደጠላት የማያይና የማይወስድ መሆኑን ነው::*

*ለነገሩ ማንንም የኅብረተሰብ ክፍል ያገለለ ሥርዓት ፍትኃዊ ሊሆን አችልም:: ፍትኃዊነትና ቅንንነት የጎደለው አሠራርና አካሄድ ደግሞ መተማመንና መግባባትን አያስገኝም:: መግባባትና መተማመን በሌለበት ሁኔታ ደግሞ ዘለቄታዊ ሰላምና መረጋጋት ከምኞት አያልፉም:: የኛም አካሄድ በተቻለ መጠን ሁሉንም ያቀፈና በእኩል የሚያይ መሆን ይኖርበታል::*

*ሕወሓት/ኢሕአዴግንም ሆነ ማንንም ፈጽሞ ያገለለ ምንም ዓይነት የሰላም ሽግግር አይኖርም:: የፖለቲካ መድረኩን ለሁሉም ተዋንያን እኩል ማደላደል የግድ ነው::*

*በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የምንለውን እንዲሰማና እንዲቀበል÷ ለወደፊቱ የጋራ ዕድላችን የምናደርገው የተቀደሰ የጋራ ብሔራዊና ወገናዊ ዓላማ ትግላችን እንዲሰምር በኅብረታችን መዝለቁ ቁልፍ ነው::*

*መንግሥት በጋራ ቆመን የምንለውን የምር ካልወሰደና ኅብረቱ በኅብረት ደረጃ እንዲሳተፍ ካልሆነ÷ የምርጫውን ጊዜ የማስተላለፍም ይሁን በዚህ ምርጫ ያለመሳተፍ ወይም ከተኮፈሰበት የሥልጣን ቦታ ማስወገድ የምንችልባቸውን ማናቸውም ዓይነት ሰላማዊ እርምጃዎች የምንወስደው በጋራና በብሔራዊ አጀንዳነት ወስደንና ተቀብለን ብቻ መሆን ይኖርበታል::*

*ኅብረቱ የሚቀጥለውን ምርጫ በኅብረት ደረጃ መሳተፍ ይኖርበታል የምንለው በተናጠል ድርጅትም ሆነ የነፍስ-ወከፍ ድርጅቶች የሚያደርጉትን ተሳትፎና ውድድር ኅብረቱ በበላይ ሆኖ በማቀናበር/በመምራት የምንፈልገውን የጋራ ድል ስለማያስገኝልን ነው::*

*ይኽ ደግሞ በተደጋጋሚ እንዳልነው እየተቃጠለች ያለች አገራችንና እየደቀቀ ያለ ሕዝባችን ከሚገኙበት የተወሳሰበና አሳዛኝ ሁኔታ በመነሳት ነው::*

በዚህ የጋራ አካሄድ ምርጫውን በድል ስንቋጭ ደግሞ የምንከተለው የበሰለና የተሻለ ወደ መጨረሻው ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ወደሚያደርግ የጋራ ግባችን የሚወስደንን ለሁላችንም የተስተካከለ የፖለቲካ ትግል ሜዳ እንዲኖረን የሚያስችለንን የአደራ መንግሥት በበጎ ፈቃዳችን እውን ስናደርግ ነው፡፡
የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኛ ከፖለቲካ ድርጅቶች ከዚህ ያነሰ አይጠብቅብንም፡፡
በኛ እምነት ትግላችንን በዚህ የጋራ አካሄድና ስምምነት ከመራነው ብቻ ነው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በመንግሥት ደረጃ መሰናክልና መተናኮል ሳይገጥመው ሁሉም ከያዘውና ከቆመበት ዓላማ ጥንካሬና ድርጅታዊ ብቃት አኳያ እራሱን መፈተን፥ ማስመስከርና ማረጋገጥ የሚችለው፡፡
አቅሙና ጉልበቱ ያለውና እውነት ለሥልጣን እበቃለሁ የሚልና የሚሻ ያኔ "ፈረሱም ይኸው ጋሪውም ይኸው " ይባልለታል፡፡
ለብዙዎች ደግሞ በሰለጠነና በሰላማዊ መንገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት ሆኖ ከማየት የበለጠ የመንፈስም ሆነ የኅሊና እርካታ አይታያቸውም፡፡

ስላመለጡ መልካም አጋጣሚዎች፥ ስላሉን የጋራ ችግሮችም ሆነ ስለ ተሠሩ ስህተቶች ማተቱ ለአንዴና ለሁሌ ይብቃን፡፡
የሁሉም ዜጎቿ ድምር ውጤት የሆነችው አገራችን ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት፡፡
ባለፉ ሥርዓቶች የደረሱ ስህተቶችም ይሁኑ በደሎች የጋራ የሆኑ ብሔራዊ ውርደቶቻችን ናቸው፡፡
የደረሱ በደሎችን አድበስብሰን እንለፍ፥ እንዳልደረሱም ይሁን እንዳልነበሩ እንቁጠር ለማለት አይደለም፡፡ በጭራሽ፡፡ ይኸማ "አድበስብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" የሚለውን የአበው ማስጠንቀቂያ መግደፍ ይሆናል፡፡ የወደፍት እይታችንን አያጨግግብን ለማለት ነው፡፡
ማናችንም ወደኋላ አጠንጥነን ስህተቱን እንዳልነበር ማድረግ አንችልም፡፡ ማድረግ የምንችለውና የሚገባን ያ ሁኔታ በምንም መልኩ እንዳይመለስ ብቻ አይደለም የወደፊት ዕድላችን በዚያ ሰቆቃ እንዲቀረጽ፥ እንዲገለጽና እንዲወሰን ዕድል አለመስጠት ይሆናል፡፡
የወደፊት የጋራ ዕድላችንን የጋራ ኅልውናችንና ተስፋችን ይቅረጹት፥ ይግለጹት ለማለት ነው፡፡ ይኸም በኅብረታችን ይረጋገጥ፡፡

ያለፈው አንድ ዓመት የሚሆን ወርቃማ ለውጥ ማስገኛ የትግል ጊዜ እንደገና እንዲጠወልግ፥ የሕዝባችን ተስፋ እንዲጨግግና ሰቆቃው እንዲቀጥል አንፍቀድ፡፡
በዚህ የትግል ወቅት በማንም ይሠራ በማን ማንኛውንም ስህተትም ይሁን ድክመት፥ በአብዛኛው በጎ ለመሥራት ከመሞከር የተፈጸመ ቅን ስህተት ስለሚሆን በቀና ልቦና የጋራችን አድርገን እንየው፡፡

ኅብረሕዝብ ኢትዮጵያ አሁንም ወደፊትም ኅብረቱ በውስጡ ያሉትን ችግሮች በውይይት ፈትቶ የሚጠበቅበትን ብሔራዊና አገራዊ ኃላፊነት በሚገባ ይወጣ ዘንድ የሚቻለውንና አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ከማድረግ ላፍታም ወደ ኋላ እንደማይል ማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

ኅብረታችን ለጋራ ኅልውናችን መሠረት ነው!
አንድነታችን በኅብረታችን ይረጋገጣል!!
ኅብረት ኃይል ነው!!!
ከግል ጥቅም የሕዝብ ጥቅም ይቅደም !!!!

**ሰኔ** 1996 ዓ/ም